ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ረቡዕ 82ኛ ዓመት ቁጥር 151 የካቲት 1 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከማልታ ጠቅላይ ሚኒስትር ሮበርት አቤላ ጋር ተወያዩ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶክተር) ከማልታው ጠቅላይ ሚኒስትር ሮበርት አቤላ ጋር በተለያዩ የትብብር መስኮች ዙሪያ ተወያዩ።


ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው በአውሮፓዊቷ ሀገር ማልታ ሲደርሱ በማልታ ጠቅላይ ሚኒስትር ሮበርት አቤላ ይፋዊ የአቀባበል ሥነ ሥርዓት እንደተደረገላቸው ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መረጃ "የማልታ ጠቅላይ ሚኒስትር እና መንግሥታቸው ላደረጉልን ደማቅ አቀባበል አመሰግናለሁ" ብለዋል።

ሁለቱ ሀገሮች በተለያዩ ዘርፎች እርስ በርሳቸው የሚማሩት ብዙ ነገር አለ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የዛሬው ውይይት የተለያዩ የትብብር መስኮችን ይበልጥ አጠናክሯል ሲሉም አስታውቀዋል።

ሁለቱ መሪዎች እና የልዑካን ቡድኖቻቸው በንግድ፣ ኢንቨስትመንት፣ ቱሪዝም፣ በባሕር፣ በሎጂስቲክስ እና በጸጥታ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ትብብር ማሳደግን ጨምሮ የሁለትዮሽ ግንኙነት የተዳሰሰበት ውይይት ማካሄዳቸው

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# «ኢትዮጵያ ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ትኩረት ሰጥታ እየተንቀሳቀሰች ነው»

- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- አገራችን በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ላይ ትኩረት ሰጥታ በመንቀሳቀስ ስኬታማ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ።

የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት ከወሎ ዩኒቨርሲቲ እና ከኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት ጋር በመተባበር "ጠንካራ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ጥራት ላለው ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰት" በሚል መሪ-ቃል በኮምቦልቻ ከተማ ምክክር አድርጓል።

በመድረኩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚዳንት ዶክተር ይልቃል ከፋለን ጨምሮ በርካታ የመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች

«ኢትዮጵያ ለኢኮኖሚ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ባንኩ በትግራይ ክልል በሚገኙ 31 ቅርንጫፎች የተሟላ አገልግሎት መስጠት ጀመረ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል በሚገኙ 31 የባንኩ ቅርንጫፎች የተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት መጀመሩን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ በትግራይ ክልል በመቀሌ እና በዙሪያው ባሉ ከተሞች የሚገኙ 31 የባንኩ ቅርንጫፎች የተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን በትዊተር ገፃቸው አስታውቀዋል።

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በይፋዊ የትስስር ገጹ እንደገለጸው፤ በትግራይ ክልል ተከስቶ በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት ተቋርጦ የነበረው የባንክ አገልግሎት በዛሬው ዕለት በድጋሚ ተጀምሯል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከብሔራዊ ባንክ ለክልሉ የተላከውን ብር ለቅርንጫፎች በማከፋፈል በመቐለ ከተማ በሚገኙት ሁሉም ቅርንጫፎች እንዲሁም በዓብይ ዓዲ፣ ማይ ለሚን፣ ሳምረ፣ ግጀት፣ ሃይቂ መስሓል፣ ወርቅ አምባ፣ አፅቢ እና አጉላዕ በሚገኙ በአጠቃላይ 31 ቅርንጫፎች የተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

በተጨማሪም በዓዲግራት፣ ውቅሮ፣ ፍረወይኒ፣ ሓውዜን፣ ዓዲጉዶም፣ ሒዋነ፣ ዓዲሽሁ፣ መኾኒ፣

ባንኩ በትግራይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ አቤ ሳኖ



## ኮንትሮባንድ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ኮሚሽኑ አስታወቀ

- ከማዕድን የሚገኘው ገቢ 63 በመቶ ቀንሷል

ገጽ 4

















ደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት




የኦሮሚያ ልማት ማህበር ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት




ወላይታ ሊቃ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት

# ሙሉ ተማሪዎቻቸውን ለድል ያበቁ መካነ ትምህርቶች

**በዳግማዊት ግርማ**

የወላጅ ተስፋ ነገ በተባለች በልጆቹ የቀን ሰማይ ላይ ርቃ የተሰቀለች ዳቦ ናት። በአብራኩ ክፋይ መማር ላይ የዛሬን ፈተና የሚሻገር እልፍ ወላጅ አለ። አሳዳጊ ልጅን አስተምሮ ለወግ ለማብቃት የሚወጣው እልፍ ዳገት የሚወርደው የትዬለሌ ቁልቁለት አለው።

ትልልቅ ነን ባይ አገራት ከነሱ አናሾች ላይ የሚኩራሩት በቁጥራቸው በተጠጉ ምሑራን ብዛት ልክ ነው። መማር ከልክ የሚልቅ ከመለኪያ በላይ ነው። ብቸኛ ባይሆንም የሀገርን ልዕልና መሠረት ጣይ ክዋኔዎች መሐል አንዱ ትምህርት ነው። በተለይ በዘመናችን ሰው በመሆን ልኬት ውስጥ መማር የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል። መማር በኩራት በአደባባይ አንገትን ቀና አድርጎ ለመሄድ መንገድ ጠራጊ ነው። ሰው የእውቀት አድማሱን ባሰፋ ቁጥር ዓለም ለመኖር ምቹ ትሆናለች።

ከዚህ ትምህርት ከተባለ ጉዳይ ተፈጥሯዊ ሂደት ውስጥ የማይቀረው አካል ደግሞ ፈተና ነው። በፈተና ላይ ፈታኝ፣ አላፊና ወዳቂ አካላት አሉ። ፈተና ያወቀውን ካላወቀው፤ ብቁውን ካልበቃው አንጥሮ መለያ ወንፊት ነው። በዚህም ወደከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለማለፍ የተደረገውን ፈተና ጉዳይ ልናወጋችሁ ወደድን።

ዘንድሮ ውጤታቸውን የተቀበሉ ተማሪዎች የአዲስ ሂደት ጅማሬ አርፎባቸዋል። የተገኘው ውጤት አስደንጋጭ ቢሆንም በትምህርት ዙሪያ የሀገሪቷን ቁመና ያመላከተ ነበር።

ለበርካታ ዓመታት ተለምዶ የነበረው ተገፍቶ የማለፍ አባዜ ዘንድሮ ራሱ ፈተና ተጋረጠበት፡፤ በብዙዎች ልብም ውጤቱ አሁን ካለው የተለየ ይሆናል ተብሎ ታስቦ ነበር። ከአንድ ሺህ የሚልቁ ተቋማት ተማሪዎቻቸው ሙሉ በሙሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ደጃፍ ለመርገጥ የሚያስችል ውጤት አልነበራቸውም። ይህ ዓይነቱ ነገር እንግዳ ስሜት ፈጠረ። በዚህ ሰማይ የተደፋ ያህል ከባድ በመሰለው የውጤት ናዳ መሐል ግን ጥቂት አዳሪ ትምህርት ቤቶቻችን ተስፋ እንዳንቆርጥ አድርገውናል። ለአብነትም ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ ተማሪዎቻቸውን ሙሉ በሙሉ ማሳለፍ ከቻሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሦስት ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን እናስተዋውቃችሁ።

ከነዚህ መካከል አንዱ የይሁኔ ወልዱ መታሰቢያ ደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ነው። ከሰባት መቶ ነጥቦች 666 ያህሉን መመለስ በቻለው በተማሪ ሚኪያስ አዳነ አማካኝነት የዘንድሮውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ትልቁን ውጤት በእጁ ጨብጧል። ከ20 በላይ የሚሆኑት የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ውጤትም ከ600 በላይ ሆኗል።

የትምህርት ተቋሙ የካቲት 01 ቀን 2011 ዓ.ም ነበር አገልግሎት የጀመረው። 29 ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር የግንባታ ወጪ ተደርጎበት ተመሥርቷል። የትምህርት ተቋሙ በሰሜኑ ጦርነት 23 ሚሊዮን ብር በላይ ጉዳት ደርሶበትም ነበር።

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በለጠ ኃይሌ ለኢፕድ በሰጡት አስተያየት ተማሪዎቹ ለማደርያነት የሚያስፈልጋቸው ነገሮችም ያልተሟላላቸው በርካታ እንደሆነ አውግተውናል። በአዳሪ ትምህርት ቤቱ የሚያስተምሩ መምህራን በሙሉ በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቁና ውጤታቸውም ከሦስት ነጥብ አምስት በላይ የሆኑ ብቻ መሆናቸውንም አጫውተውናል።

የትምህርት ሚኒስቴር ፈተናውን በሚመለከት የወሰደው ርምጃም አድናቂ ናቸው። ተማሪ በጥራት ባይፈተን ሁሉም እንደሚገባው ማግኘት አይችልም ነበር ባይ ናቸው።

ሌላው የብርቱዎቹ ቤት የኦሮሚያ ልማት ማህበር ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ነው። ተማሪ ሮቤራ አስመራ የትምህርት ቤቱን ከፍተኛ ውጤት 652 አስመዝግቧል። ማህበሩ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን በመክፈት ሥራ ላይ ተጠምዶ ከርሟል። ትምህርት ቤቱ ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ብቻ ሳይሆን በሙሉ ማሳለፍም የለመደው ነገር ነው።

የማኅበሩ የቦርድ ሰብሳቢ ደግሞ አቶ አባ ዱላ ገመዳ ናቸው። ሰብሳቢውና የትምህርት ማኅበረሰቡ ከፍተኛ ውጤት ባስመዘገቡ ተማሪዎቻቸው ተደስተዋል። ተማሪዎቻችንን እንኮራባቸዋለን። ጥያቄያችን ያልፉ ይሆን የሚለው ሳይሆን ከስድስት መቶ በላይ ስንት ያመጣሉ የሚለው ነው ይላሉ።

ተቋሙ በኅብረተሰቡ የእኔ ነህ ተብሎ የሚደገፍ ነው። የምሥራቅ ሸዋ ዞን ማኅበረሰብ አባላት ለትምህርት ቤቱ አለንልህ ባይ ናቸው። ለትምህርት ቤቱ ከተባሉ እናቶች መቀነታቸውን አባቶች ኪሳቸውን ይፈትሻሉ። ጤፉን ከማጀታቸው ከብቱን ከበረታቸው ይዘው ተማሪዎቻቸውን ይደግፋሉ። ባለ ከፍተኛ ውጤት ተማሪዎችንም እንኳን ደስ ያላችሁ ብለዋል።

ሌላኛው የአስደናቂ የተማሪዎች ምንጭ በወላይታ ልማት ማኅበር (ወልማ) የተቋቋመው ትምህርት ቤት ነው። የዘንድሮ ከፍተኛ ውጤትም 643 ሆኖ ተመዝግቧል። በትምህርት ቤቱ ደረጃ የአንድ ተማሪ ውጤት ብቻ 378 ዝቅተኛ ውጤት ሆኗል።

በውጤቱ ምን ተሰማችሁ ስንል የትምህርት ቤቱን ርዕሰ መምህር አወራን። አቶ ማቱሳላ ጎና ይሰኛሉ። እስከዛሬ በምድር ላይ የአስራ አምስት ዓመታት ቆይታን ያደረገው ትምህርት ቤቱ ላለፉት 10 ዓመታት ሊቆችን ሲያፈራ የኖረ ነው አሉን። ተማሪዎቹ በቀለም ትምህርት ብቻ ሳይሆን በሥነምግባርም የታነፁ ናቸውም ይላሉ።

# የፌዴራል መንግሥትና ባለሥልጣኑ በትብብር ለመሥራት የጋራ ፎረም መሠረቱ

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል መንግሥትና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በትብብር ለመሥራት የሚያስችላቸው የጋራ ፎረም በትናንትናው እለት መሠረቱ።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ጋር በመተባበር ከፌደራል መንግሥት ጋራ ለመሥራት ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮች በተገኙበት የመመሥረቻ ጉባኤ በትናንትናው እለት ተካሂዷል ።

በጉባኤው ላይ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ጂማ ዲልቦ እንደገለፁት፤ ባለሥልጣኑ ከፌዴራልና ከክልል አስፈጻሚ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሠራር በመዘርጋት ውጤታማ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ሲሆን አሁን በፌዴራል ደረጃ የተመሠረተው መድረክ ሴክተሩን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመምራት ያስችላል ።

አቶ ጂማ የምክክር መድረኩ ተቀራርቦ ለመመካከርና በዘርፉ የሚታዩ ውስንነቶችን ለማረም በተለይም የሀብት ብክነትና የሥራ ድግግሞሽን ከመቅረፍ ባሻገር ያለንን ውስን ሀብት ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ተጠቅመን በፈጠነ ሁኔታ ከድህነት እንድንወጣ ያግዛል ብለዋል።

የሲቪል ማኅበረሰቡም የዘርፉን የእንቅስቃሴ አድማስ በማስፋት ብሎም ከዚህ በፊት የነበሩትን የፕሮጀክት ስምምነት መጓተት በመቅረፍ ከፌዴራል እስከ ክልል በተናበበ መልኩ ውጤታማ ተግባራትን በማከናወን የሕዝባችንን የላቀ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

በመሆኑም የምክክር መድረኩ ሊኖረው የሚችለውን ሀገራዊ ፋይዳ በመገንዘብ ሁሉም የፌደራል የመንግሥት ተቋማት ፣የሥራ ኃላፊዎች እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አመራሮች ለፎረሙ ውጤታማት የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪ አስተላልፈዋል።

ዘላቂ ሰላምና ልማትን ለማረጋገጥም ሆነ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደርን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመገንባት ሁሉን አካታች የትብብር ሥርዓት ማደራጀት የግድ ነው ያሉት የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር አቶ ሔኖክ መለሰ ፣ይህንን እውን ከማድረግ አንጻር ይህ በፖሊሲ እና እስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የፌዴራል የሲቪል ማኅበረሰቦች ድርጅቶችና የመንግሥት ትብብር መድረክ እንደተቋቋመ ተናግረዋል።

አቶ ሄኖክ በተጨማሪም የሲቪል ማኅበረሰብ ገለልተኛ በሆነ አቋም፣ መርሕን የተከተለ አሠራር ለመፍጠር ሀገራዊ ፋይዳው ከፍተኛ እንደሆነ ገልፀው፣ ምክር ቤቱ ለዚህ የምክክር መድረክ ያለሰለሰ ድጋፍ በመስጠት የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት በቁርጠኝነት እንደሚሠራ ተናግረዋል ።

በዚህ መድረክ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የፍትሕ ሚኒስትር ዲኤታ አቶ ፍቃዱ ጸጋ እንደገለፁት ፣ መድረኩ ያለውን ውስን ሀብት እና የሰው ኃይል በተናጠል ከመሥራት ይልቅ ለጋራ ዓላማ በተገናዘበ መንገድ በትብብር ለመሥራት ትልቅ ሚና አለው ሲሉ ተናግረዋል።

በተለይም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ውስጥ የዜጎችን ጥቅም ለማረጋገጥ ከፌደራል መንግሥት ተቋማት ጋር በትብብር በመሥራት የማይተካ ሚናችሁን እንደምትወጡ እና ከዚህ መድረክ ምሥረታ በኋላ ወቅታዊ ግንኙነቶችን በማድረግ የዜጎችን ተጠቃሚነት ወደላቀ ደረጃ እንደምታደርሱ እምነቴ ነው ሲሉ ተናግረዋል።



# በባቱ ለመጀመሪያ ጊዜ 540 ሄክታር መሬት ላይ የበጋ መስኖ ስንዴ ለምቷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በምሥራቅ ሸዋ ዞን ባቱ ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ 540 ሄክታር መሬት ላይ የበጋ መስኖ ስንዴ ማልማት መቻሉን የከተማው ግብርና ክላስተር ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

የባቱ ከተማ ግብርና ክላስተር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ እንድሪስ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በአካባቢው የሚገኘው አርሶ አደር የበጋ መስኖ ስንዴ እያለማ ያለው በኩታ ገጠም ነው። የደንበል ሐይቅን በመጠቀም 500 ሄክታር ስንዴ ለማልማት ታቅዶ እስከ አሁን 540 ሄክታር ለምቷል። በዚህም ሁለት ሺህ አባወራዎች ተሳትፈዋል።

በባቱ ከተማ አርሶ አደሩን በምግብ እህል እራሱ ለማስቻል እንዲያግዝ እና ስንዴን ለውጪ ገበያ መላክ እንዲቻል ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአምስት መቶ በላይ ሄክታር የበጋ መስኖ ስንዴ ያሉት አቶ እንድሪስ፤ በባቱ ከተማ ከዚህ በፊት አርሶ አደሩ ስንዴን በበጋ መስኖ የማልማት ልማድ ያልነበረው ቢሆንም አሁን የተጀመረው ስንዴን በመስኖ የማልማት እንቅስቃሴ መሠረት በማድረግ በከተማው ምቹ ቦታዎች መረጣ ተካሂዶ የበጋ መስኖ ስንዴ በመልማት ላይ ይገኛል ብለዋል።

የባቱ ከተማ ግብርና ክላስተር ቢሮ በዚህ ዓመት ብቻ በበጋ መስኖ ከ540 ሄክታር መሬት በማልማት ወደ 18 ሺህ ኩንታል ስንዴ ለማምረት ዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ገልጸውም፤ ከበጋ መስኖ ስንዴ 81 ሚሊዮን ብር ለማግኘት እየተሠራ እንደሆነ አብራርተዋል።

እንደ ኃላፊው ገለፃ፤ አርሶ አደሩ መስኖን በመጠቀም ለመጀመሪያ ጊዜ በኩታ ገጠም አሠራር በሚከናወነው የስንዴ ልማት ከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ ነው። መንግሥት 55 የውሃ መሳቢያ ፓምፖች፣ 680 ኩንታል ምርጥ ዘር ስንዴ፣ 540 ኩንታል ማዳበሪያ እና የምርት ግብዓት የማሟላት ሥራ ሠርቷል ብለዋል።

ይህም ወጣቱን ወደ እርሻ ሥራ በማስገባት በምግብ ሰብል እራሱን እንዲችልና በአንድ ቦታ ተረጋግቶ በመኖር ቋሚ የሆነ የተሻለ ሕይወት እንዲመራ ያስችለዋል ሲሉ ገልጸዋል።

በተለይ በአሁኑ ወቅት በከተማው አስተማማኝ ሰላም መኖሩን የጠቆሙት አቶ እንድሪስ፤ ካለው ሰፊ መሬት ጋር በተያያዘ በግብርና መስክ መሳተፍ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ እንዳለ ተናግረዋል።

# በትግራይ ክልል ከሰላም ስምምነቱ በኋላ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎች ውሃ አግኝተዋል

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የነበረው ጦርነት በስምምነት ከተቋጨ በኋላ በትግራይ ክልል 1ነጥብ3 ሚሊዮን ዜጎች በድጋሚ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ መሆናቸው ተገለፀ። በጦርነቱ የተጎዱት የአማራ፣ የአፋር እና የትግራይ ክልል የውሃ መሠረት ልማቶችን ለመጠገን 3ነጥብ8 ቢሊዮን ብር ወጪ እንደሚጠይቅም ተጠቁሟል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጅነር ሃብታሙ ኢተፋ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ከነበረው ጦርነት ጋር በተያያዘ በአማራ፤ አፋር እና ትግራይ ክልል በውሃ መሠረተ ልማቶች ላይ የከፋ ጉዳት ደርሷል።

በአሁኑ ወቅት እነዚህን በመጠገን ወደ አገልግሎት የማስገባት ሥራው በሰፊው እየተከናወነ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በአማራ እና አፋር ክልል ያሉት የውሃ ቢሮዎች በሥራ ላይ በመሆናቸው መጠነኛ ድጋፍ በማድረግ መሠረተ ልማቶቹን በመጠገን ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል ብለዋል። በትግራይ ክልል ደግሞ ተቋሙ ባለመኖሩ በልዩ ሁኔታ ሚኒስቴሩ በራሱ ገብቶ እየሠራ ሲሆን አጋር አካላትን ጭምር በማስተባበርም በትኩረት እየተንቀሳቀሰ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ በትግራይ ክልል በጦርነቱ ሳቢያ የውሃ መሠረተ ልማት ወድሞባቸው የነበሩ 76 ቦታዎች ላይ በተሠሩ የመሠረተ ልማት ጥገና ሥራዎች 1ነጥብ3 ሚሊዮን የሚሆኑት ዜጎች በድጋሚ የንጹሕ መጠጥ ውሃ አግኝተዋል። ለዚህም ከሚኒስቴሩ ብቻ ከ60 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ሆኗል፤ በተጨማሪም



ዶክተር ኢንጅነር ሃብታሙ ኢተፋ

ግብረ ሠናይ ድርጅቶች ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል።

እነዚህ መሠረተ ልማቶች ሲጠገኑ የትግራይ ሕዝብ ትልቅ ትብብር እያደረገ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይሁንና ይህ ከሚያስፈልገው 25 ከመቶ ብቻ የሚሸፍን በመሆኑ በርካታ ሥራዎች እንደሚቀሩም ጠቁመዋል።

በአማራ፣ በአፋር እና ትግራይ ክልሎች በጦርነት የተጎዳውን የውሃ መሠረተ ልማት ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ለማስገባት 3ነጥብ8 ቢሊዮን ብር ይጠይቃል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህን ገንዘብ ለማግኘትም በሚኒስቴሩ ሃብት የማፈላለግ ሥራ እየተከናወነ እንደሆነና የልማት ድርጅቶችና ሌሎች አጋር አካላትም ተሳታፊ እንዲሆኑ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

በጦርነት ከተጎዱት በተጨማሪ በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ መሆናቸውን የገለፁት ሚኒስትሩ፤ በ2015 በጀት ዓመት በከፍተኛ ሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋ የተጎዱ የውሃ መሠረተ ልማቶችን በመጠገን ላይ እንደሆኑም ጠቁመዋል። በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በጦርነት ከተጎዱት መሠረተ ልማቶች በተጨማሪ ጦርነት በሌለባቸው የሀገሪቱ ክፍሎችም የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ባለመሆኑ ጥያቄዎች ሲቀርቡ እንደነበር ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ በበጀት ዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ 6 ነጥብ3 ሚሊዮን ዜጎችን በመጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ እየተሠራ ሲሆን፤ በግማሽ ዓመቱ ከዕቅድ ብልጫ ያለው ሥራ ተከናውኗል። ባለፉት አራት ዓመታት የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ላይ መቀነስ የሚያመላክተው መረጃም ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ የተሻለ ውጤት እየተመዘገበ እንደሆነ ያሳያል።

2009 ዓ.ም 5ነጥብ9 ሚሊዮን፣ 2010 ዓ.ም ስድስት ሚሊዮን፣ በ2011 ዓ.ም 4ነጥብ7 ሚሊዮን፣ 2012 ዓ.ም 4ነጥብ4 ሚሊዮን፣ በ2013 ዓ.ም አራት ሚሊዮን እና በ2014 ዓ.ም 5ነጥብ3 ሚሊዮን ዜጎች በየዓመቱ የመጠጥ ውሃ ያገኙ የነበረ ሲሆን፤ ይህን እየቀነሰ የመጣ አኃዝ ከፍ ለማድረግ በትኩረት በመሥራቱ ለውጥ ተመዝግቧል። ይህም ከክልሎች ጋር ቅንጅታዊ አሠራር በመዘርጋቱና መናበብ በመቻሉ የተገኘ ውጤት ነው ብለዋል።

በመላ የሀገሪቱ የውሃ ሃብት ልማት ላይ የገፀ ምድርና ከርሰ ምድር ውሃ ብሎም የወንዝ ዳርቻዎችና ሌሎች ሃብቶችን በመንከባከብ ውጤታማ ተግባራት መከናወናቸውንም ሚኒስትሩ አረጋግጠዋል።

# ብሔራዊ ሙዚየም በርካታ ቅርሶቹን በቦታ እጥረት ምክንያት ለእይታ ማቅረብ አልቻለም

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቅርሶቹን በቂ ቦታ ባለመኖሩ ለእይታ ማቅረብ አለመቻሉን በኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ደመረው ዳኜ ገለጹ።

ሙዚየሙ ባለፉት ስድስት ወራት ከ 36 ሺ በላይ ጎብኚዎችን ያስተናገደ ሲሆን ከ900 ሺህ ብር በላይ ገቢ ማግኘቱም አቶ ደመረው ተናግረዋል።

አቶ ደመረው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በቱሪዝሙ ዘርፍ ትልቁ መዳረሻ የሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም በዓለም ላይ ከተገኙ 23 የቅድመ ሰው ዝርያዎች መካከል ቀደምት የሆኑትና ኢትዮጵያን በሰው ልጅ መገኛነት ምስክር የሚባሉት እነ ሉሲ እና አርዲ ይገኙበታል። ሙዚየሙ በርካታ ቅርሶች ቢኖሩትም በቦታ እጥረት ምክንያት ለእይታ ማቅረብ አልተቻለም።





የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም

በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች፣ ተመራማሪዎችና የተለያዩ ሀገራት ልዑካኖች ወደ ኢትዮጵያ በሚመጡበት ጊዜ ብሔራዊ ሙዚየሙን መጎብኘት እንደሚፈልጉ የተናገሩት አቶ ደመረው፤ ምንም እንኳ ቱሪስቶቹ ብዙ ነገሮችን ፍላጎት ቢያሳዩም በቦታ እጥረት ምክንያት በሙዚየሙ የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቅርሶች ማስጎብኘት እንዳልተቻለ አብራርተዋል።

ከ10 ዓመት በፊት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰው ልጅ መገኛ ሙዚየም በተለየ መልኩ አምስት ኪሎ ላይ እንዲገነባ ከ4ሺ ካሬ ሜት በላይ ቦታ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ሙዚየሙ አለመረከቡን ያወሱት ዳይሬክተሩ፤ በ2011 ዓ.ም በቦታው ላይ ለሚኖሩ ነዋሪዎች የ9 ሚሊዮን ብር ካሳ እንደ ተከፈለ ነገር ግን ቦታውን ከአራዳ ክፍለ ከተማ መረከብ አለመቻሉን ተናግረዋል።

የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሞላ ንጉስ በበኩላቸው፣ ክፍለ ከተማው ሕጋዊ የሆኑትን ነዋሪዎችን የመለየት ሥራ እየሠሩ መሆናቸውን ገልጸው፤ በተለይ በከተማዋ የሚስተዋለው የቀበሌ ቤት እጥረት ለነዋሪዎቹ ምትክ ቤት መስጠት ባለመቻሉ ለሥራው መጓተት ትልቅ እንቅፋት መፍጠሩን አመልክተዋል።

ሆኖም ግን ምትክ ቤቶቹ ሲገኙ ለነዋሪዎቹ በመስጠት ቦታውን ለሙዚየሙ ለማስረከብ እንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የሙዚየሙ ዳይሬክተር አቶ ደመረው ይህ ቢሳካ ኖሮ ሙዚየሙ የሰው ዘር ቅሪት አካሎችን በመያዝ ከዚህ በፊት ከነበረው የተሻለ ጎብኚዎችን መሳብ እና በኢኮኖሚውም ዘርፍ የተሻለ ገቢ ማስመዝገብ በተቻለ ነበር ብለዋል።

አቶ ደመረው በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሙዚየሙ ለ8 ወራት ተዘግቶ መቆየቱ፣ በወረርሽኙ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አንዳንድ ሀገራቶች ዜጎቻቸው ከሀገር እንዳይወጡ ማገዳቸው እና ላለፉት 2 ዓመታት በኢትዮጵያ በነበረው ጦርነት ሀገራቶች ኢትዮጵያን የስጋት ቀጠና አርገው መፈረጃቸው የጎብኚዎች ቁጥር ላይ ተጽዕኖ ፈጥሮ መቆየቱን ገልጸው፤ አሁን ላይ ሙዚየሙ ካለፉት ዓመታት በተሻለ መነቃቃት ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።



ዶክተር ኢንጂነር ሱልጣን ወሊ

# ከ38 ሺህ በላይ አባወራዎች የባዮ ጋዝ ኢነርጂ ተጠቃሚ ሆነዋል

**በሪሁ አረጋ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ከ38 ሺህ በላይ አባወራዎች የባዮ ጋዝ ኢነርጂ ተጠቃሚ መሆናቸውን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ። በቀጣይም የተጠቃሚዎቹን ቁጥር ከፍ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑም ተነግሯል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የኢነርጂ የልማት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ዶክተር ኢንጂነር ሱልጣን ወሊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ በኢትዮጵያ በባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ዘርፍ በተደረገው እንቅስቃሴ እስካሁን ከ38 ሺህ በላይ አባወራዎች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

ሀገሪቱ ከፍተኛ የሆነ የታዳሽ ኢነርጂ ምንጭ ባለቤትና ከፍተኛ የሆነ የኤሌክትሪክ ኢነርጂ ምንጭ ያላት ብትሆንም ዝቅተኛ የሆነ የኢነርጂ ተደራሽነት ነው ያለው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ የሆኑት ሕዝቦች ከ48 በመቶ በታች ናቸው ሲሉም ተናግረዋል።

ይህ የተጠቃሚ ቁጥር የሚያመላክተው ከ65 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ያለ ኤሌክትሪክ ኢነርጂ ተደራሽነት በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸውን ሚኒስቴር ዲኤታው ገልፀዋል።

ለዘመናዊ የኢነርጂ ምንጭና ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ቅርቦት ያለው ደግሞ ከ10 በመቶ ያነሰ ሕዝብ ሲሆን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ግን ቀሪውን 90 በመቶ የሚሆነው የሀገሪቱ ሕዝብ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ በትኩረት እየሠራ መሆኑ ተገልጿል።

የባዮ ጋዝ ኢነርጂ ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዳለውና በዋናነት ለምግብ ማብሰያነትና ለመብራት ግልጋሎት ይውላል ያሉት ሚኒስቴር ዴኤታው፣ ሰዎች ምግብ ለማብሰል የሚጠቀሙትን እንጨት ለማግኘት ደን እንዳይጨፈጭፉ በማድረግ የአፈር መሸርሸርን ይከላከላልም ብለዋል።

ሚኒስቴር ዴኤታው አክለውም፣ ባዮ ጋዝ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች እናቶችና ሕፃናት ምግብ በሚያበስሉበት ወቅት በሚፈጠረው ጭስ አማካኝነት ለዓይንና ሌሎች የለተያዩ በሽታዎች እንዳይዳረጉ በማድረግ የአየር ንብረት ብክለት እንዳይከሰት ጉልህ ሚና ይጫወታልም ብለዋል።

እንደሀገር የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂው በሀገሪቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ያለው የተጠቃሚው ቁጥር ዝቅተኛ ነው፣ ይህም የሆነው ማኅበረሰቡ ለባዮ ጋዝ ኢነርጂ ያለው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑን አመላክተዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም በቂ የማስተዋወቅና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እየሠራ እንደሚገኝ ሚኒስቴር ዲኤታው ጠቁመው፣ ሀገሪቱ ባላት የተፈጥሮ ሀብትና የቴክኖሎጂ ደረጃ ተጠቃሚ ለማድረግም የባዮ ጋዝ ኢነርጂ ለማስፋፋት እየተሠራ ነው መሆኑን ገልፀዋል።

የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊና እንዲሁም ከባቢያዊ አየር ብክለትን ከመከላከል በተጨማሪ የጤና ጉዳት የማያስከትል በመሆኑ በዘርፍ ላይ በቀጣይነት በትኩረት መሥራት መታቀዱንም አንስተዋል።

# የሕንፃ ተደራሽነት አዋጁ የአካል ጉዳተኞችን ችግር የሚቀርፍ አይደለም

*- የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማኅበራት ፌዴሬሽን*

# የችግሩ ምንጭ የሕግ ክፍተት ሳይሆን የአፈጻጸም ጉድለት ነው

*- የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር*

**አመለወርቅ ከበደ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ለአካል ጉዳተኞች ታስቦ የወጣው የሕንፃ ተደራሽነት አዋጅ የአካል ጉዳተኞችን ችግር የሚቀርፍ ባለመሆኑ መስተካከል እንዳለበት የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማኅበራት ፌዴሬሽን አሳሰበ። የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በበኩሉ ችግሩ የሕግ ክፍተት ሳይሆን የአፈጻጸም ችግር መሆኑን አስታውቋል።

የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማኅበራት ፌዴሬሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ አባይነህ ጉጆ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሕንፃዎች በሚሠሩበት ወቅት አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደረጉ መሆን እንዳለባቸው የተደነገገው አዋጅ የአካል ጉዳተኞችን ችግር የሚቀርፍ አይደለም ብለዋል።

አዋጁ ርዕሱ ላይ የአካል ጉዳተኞች የሕንፃ ተደራሽነት አዋጅ የሚል ቢሆንም፤ የተደነገገው ሀሳብ አካል ጉዳተኞችን ሳይሆን ጉዳት አልባውን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

አዋጁ የአካል ጉዳተኛው ተሳትፎበት እና መክሮበት የወጣ አለመሆኑን የገለጹት አቶ አባይነህ፤ አንድ ሕንፃ ሲሠራ ከሦስት ወለል በላይ ከፍታ ካለው አሳንሰር እንዲኖረው ቢያዝም ተግባራዊ እየተደረገ አይደለም ሲሉ ገልጸዋል።

የአካል ጉዳተኞች የሕንፃ ተደራሽነት አዋጅ ተብሎ ቢደነግግም አካል ጉዳተኞችን እየረዳ የሚገኝ ሕግ አይደለም ያሉት አቶ አባይነህ፤ በመሆኑም የአካል



አቶ አባይነህ ጉጆ

ጉዳተኞችን የሕንፃ ተደራሽነት የሚያረጋግጥ ጠንካራ አስገዳጅ ሕግ መውጣት ይኖርበታል ሲሉ በአፅንዖት አስገንዝበዋል።

የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ስንመለከት አሳንሰር የተገጠመላቸው ባለመሆናቸው አካል ጉዳተኞች ለችግር ተዳርገዋል ያሉት ኃላፊው፤ የዚህ ጥያቄ በሚነሳበት ወቅት ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ ተሰጥቶ መሬት ላይ ያሉትን ቤቶች እንሰጣለን የሚል ምላሽ ቢሰጥም፣ አካል ጉዳተኛው ለተለያዩ ጉዳዮችና ማኅበራዊ ግንኙነቶች በሚንቀሳቀስበት ወቅት አሳንሰር ባለመኖሩ አካል ጉዳተኛው መቸገሩ እንዳልቀረ ተናግረዋል።

አቶ አባይነህ፤ ሕንፃዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ለማስቻል በወጣው አዋጅ ትርጉማቸው አሻሚ የሆኑ አገላለፆች እንዳሉም አክለው ተናግረዋል። የመንግሥት አቅም በፈቀደ መልኩ የአካል ጉዳተኛውን ይረዳል የሚል አገላለፅ አዋጁ ላይ መስፈሩም የአካል ጉዳተኞች ሰብዓዊ መብት እና ክብር እየተነካ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ 20 ሚሊዮን አካል ጉዳተኞች ያሉባት ሀገር እንደመሆኗ ችግሩን ለመቅረፍ ግልጽ፣ ጠንካራና አስገዳጅ ሕግ ያስፈልጋል ሲሉም ገልፀዋል።

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ አብዱ ጀማል በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ችግሩ ያለው አዋጁ ላይ ሳይሆን አፈፃፀም ላይ ነው። በክልሎችም ሆነ በከተማ አስተዳደሮች ያለው ችግር ሕጉን ጠብቆ ያለመሥራት ነው።

አዋጁ ላይ ሕንፃ ሲሠራ ለአካል ጉዳተኞች ምን ምን ነገሮችን ማሟላት እንዳለበት ከመጸዳጃ ቤቶች ጀምሮ አዋጁ ላይ ተጠቅሷል። የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሥራ ሕግ አውጥቶ በመስጠት እንዲፈፀም ድጋፍና ክትትል ማድረግ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የግንባታውን ንድፍ ካፀደቁ እና ፈቃድ ከሰጡ በኋላ የግንባታውን እያንዳንዱን ሂደትና አፈፃፀም መመልከት፣ መቆጣጠር የየከተማው የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ድርሻ ነው የሚሆነው ሲሉ አስረድተዋል።

የሚገነባው፣የሚያስገነባው፣ ፈቃድ የሚሰጠው አካል የኔ ብሎ ያለማየት ችግር አለ። ሁሉም አካል የኔ ብሎ ኃላፊነት እንዲወስድ ያደገ አስተሳሰብ መፍጠር ያስፈልጋል ሲሉም ገልፀዋል።

# ኮንትሮባንድ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ኮሚሽኑ አስታወቀ

## - ከማዕድን የሚገኘው ገቢ 63 በመቶ ቀንሷል

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር የሚደረገው ጥረት በከፍተኛ ደረጃ ቢጨምርም ችግሩ ሀገሪቱን ለከፍተኛ አደጋ በሚያጋለጥ ደረጃ መጨመሩን ጉምሩክ ኮሚሽን አስታወቀ። በኮንትሮባንድ ሳቢያ ከማዕድን የሚገኘው ገቢ 63 በመቶ መቀነሱም ታውቋል።

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የተከናወነው የፀረ ኮንትሮባንድ ንቅናቄ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ቢመጣም ችግሩም በከፍተኛ መጠን እያደገ መጥቷል።

ለውጡን ተከትሎ የተወሰደ የመቆጣጠር ውጤት መኖሩን አቶ ደበሌ ጠቁመው፤ በ2011 ዓ.ም ኮሚሽኑ አጠቃላይ በሕገወጥ ንግድና በሕጋዊነት ሽፋን ሲንቀሳቀስ የነበረ የ9 ነጥብ8 ቢሊዮን ብር ፣ በ2012 የ26 ነጥብ2 ቢሊዮን ብር፣ በ2013 ዓ.ም 36ነጥብ7 ቢሊዮን ብር፣ በ2014 ዓ.ም ደግሞ 50 ቢሊዮን ብር እንዲሁም በ2015 ዓ.ም በስድስት ወር ውስጥ ብቻ የ40 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ኮንትሮባንድ መቆጣጠር ተችሏል ብለዋል።

የመቆጣጠር አቅማችን ቢያድግም በዚያው ልክ ኮንትሮባንድ መስፋፋቱ ሀገሪቷ ላይ ከፍተኛ ሥጋት መደቀኑንም ኮሚሽነሩ አስታውቀዋል።

ኮሚሽነር ደበሌ እንደተናገሩት፤ በቢሊዮን የሚቆጠር ሃብት በኮንትሮባንድ መልክ ለማስገባትና ከሀገር ለማስወጣት ጥረት ይደረጋል፤ ሆኖም ይህን የሀገር ስጋት ለመቆጣጠር አስፈላጊው ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

የሀገርን ገቢ በከፍተኛ ሁኔታ እያሳጣ የሚገኘውን የኮንትሮባንድ አደጋ ለመከላከል ኅብረተሰቡ የሚያደርገውን ተሳትፎ እንዲያጠናክርም ጥሪ አቅርበዋል።

በተጨማሪም ማዕድን ዘርፍ ላይ ያንዣበበው ኮንትሮባንድ አሳሳቢ መሆኑን የገለጹት ኮሚሽነር



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ

ደበሌ፤ ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ከምታገኝባቸው ዘርፎች አንዱ ማዕድን ቢሆንም በኮንትሮባንድ የተነሳ ገቢው ማሽቆልቆሉን ተናግረዋል።

ባለፈው በጀት ዓመትም በኮንትሮባንድ ንግድ የተነሳ ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት ከሚገባት 63 በመቶ መቀነሱን አብራርተዋል።

በተለያየ መንገድ የኢትዮጵያን ማዕድናት በተለይም ወርቅን በሕገወጥ መንገድ ከሀገር በማስወጣት የተሳተፉ አካላት የማዕድን ገቢው እንዲቀንስ ምክንያት መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል የዕፅ ኮንትሮባንድም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መሆኑን የጠቆሙት ኮሚሽነሩ፤ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ዕፅ መበራከትና በትምህርት ቤቶች ጨምሮ የሚስተዋለው የዕፅ ዝውውር ለኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ ደቅኗል ብለዋል።

“በጣም አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታም የተለያዩ አደንዛዥ ዕፆች ባልተለመደ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ በኮንትሮባንድ እየገቡ ነው። በየብስ እና በአየር የሚገባውን ዕፅ ለመቆጣጠር ጥረት ቢደረግም በሀገር ውስጥ ደግሞ ‹‹ካናቢስ›› በሕገወጥ መንገድ እየተመረተ ነው” ብለዋል።

የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውሩ በርካታ ሰዎችን ለማኅበራዊ ምስቅልቅል እየዳረገ በመሆኑ ከወዲሁ ቁጥጥሩን ማጠናከር ይገባል ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

እንደ ኮሚሽር ደበሌ ገለፃ፤ ከኮንትሮባንድ ቁጥጥሩ ባለፈ ኮሚሽኑ የገቢ ንግድ ጉምሩክ ሥርዓትን በተመለከተ በሰፊው እየሠራ ይገኛል።

በስድስት ወራት 90 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር የጉምሩክ ገቢ ለማምጣት ታቅዶ 87ነጥብ1 ቢሊዮን ብር ተሰብስቧል። ይህ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ34 ቢሊዮን ብር ብልጫ አለው ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ተቋሙ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ትልቅ ትኩረት የሰጠ ሲሆን በአንድ የመስኮት አገልግሎት በመተግበሩ በአንድ ዓመት ብቻ ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ኪሳራ ማዳን ተችሏል ሲሉ ኮሚሽነሩ ገልጸዋል።

ከዚህ ባለፈ መንግሥት የኑሮ ውድነትን ለማቃለል በሚያደርገው ጥረትም ኮሚሽኑ ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

በስድስት ወራት ብቻ 44 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የተለያዩ ምርቶችና ማሽነሪዎች ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቷል። ከዚህ ውስጥ ደግሞ 10 ቢሊዮን የሚሆነው ምግብና ምግብ ነክ ላይ የዋለ ነው ሲሉም አብራርተዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ የግብርናው ምርት የበለጠ እንዲያድግ የሚረዱ ማሽነሪዎችንና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ በመደረጉ ኮሚሽኑ ለምርታማነት ማደግና ለሥራ ዕድል ፈጠራ የበኩሉን ሚና እየተወጣ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

# ጠቅላይ ሚኒስትር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ታውቋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ከትናንት በስቲያ በጣሊያን የሥራ ጉብኝት በማድረግ ከፕሬዚዳንት ሰርጂዮ ማታሬላ እና ከጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒጋር መምከራቸው የሚታወስ ነው።

ከአምስት ዓመት በፊት ኢትዮጵያና ማልታ ያለተጨማሪ ቀረጥ ምርቶችን ለማስገባት ስምምነት አድርገዋል።

# ባንኩ በትግራይ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ማይጨውና አካባቢው በሚገኙ ቅርንጫፎች በቅርብ ሰዓታት ውስጥ ባንኩ የተሟላ አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምር ከመቐለ ዲስትሪክት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል ሲል ባንኩ በማኅበራዊ ትስስር ገጹ አሳውቋል።

የኢትዮጵያንግድባንክሥራየጀመረባቸውአካባቢዎች የቴሌ መሠረተ ልማት ዝርጋታዎች የተሟላባቸው ሲሆኑ፤ የተወሰኑ የቴሌ መሠረተ ልማት ጥገና ባልተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች በቅርቡ ሙሉ በሙሉ አገልግሎት ለመስጠት ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቁ አስታውቋል።

በሌላ በኩል የባንኩ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አልሰን አሰፋ ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት እንደገለጹት፥ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከብሔራዊ ባንክ ለትግራይ ክልል የተላከውን ብር ለቅርንጫፎች አከፋፍሏል።

በዚህ መሠረትም ባንኩ በመቀሌ ከተማ በሚገኙት ሁሉም ቅርንጫፎች እንዲሁም በዓብይ ዓዲ፣ ማይ ለሚን፣ ሳምረ፣ ግጀት፣ ሃይቂ መስሓል፣ ወርቅ አምባ፣ አፅቢ እና አጉላዕ በሚገኙ 31 ቅርንጫፎች የተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

# «ኢትዮጵያ ለኢኮኖሚ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ተገኝተዋል።

መድረኩን በንግግር የከፈቱት አቶ ደመቀ መኮንን፤ አገራችን በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ላይ ትኩረት ሰጥታ በመንቀሳቀስ ከሌሎች አገሮችና ዓለምአቀፋዊ ድርጅቶች ጋር ስኬታማ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ትብብሮችን በማጠናከር ተጠቃሚነቷን ለማሳደግ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ሀገራችን በተፈጥሮ ሃብት የታደለች ብትሆንም የማምረት አቅሟን አሳድጋ በኢኮኖሚው መስክ ጠንካራ የተወዳዳሪነት ቁመና ላይ ነች ብሎ ለማለት አያስደፍርም ሲሉም ተናግረዋል።

ለዚህም መንግሥት የትኩረት ብዝኃ-ዘርፎች ማለትም፣ ግብርና፣ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ፣ ማዕድን፣ ቱሪዝም እና ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ለኢኮኖሚ እና መዋቅራዊ ሽግግር መረጋገጥ ያላቸውን ድርሻ መሠረት በማድረግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ከተፈለገ ሰላሟ የተጠበቀ እና ደህንነቷ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን እውን ማድረግ በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን በመግለፅ፤ ሰሞኑን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የተከሰተው ችግር እጅግ አሳሳቢና በከፍተኛ ብልህነትና ብስለት መፍታት የሚጠይቅ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

የሃይማኖቱን መሠረታዊ መርሆዎችን በመጠበቅና መደመጥ ያለባቸውን ድምፆች በመውሰድ መፍትሔ መሻትን በመላበስ ከስሜትና ከእልህ በፀዳ መልኩ በአባቶች ጥበብና ፀጋ እንዲሁም በአማኞች አስተውሎት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሀይማኖት አንድነቷ ተከብሮና ተጠብቆ ትቀጥላለች ነው ያሉት አቶ ደመቀ፡፡

ከዚህ ውጭ ለፖለቲካም ሆነ ለሌሎች ፍላጎቶች መጠቀሚያ የማድረግ አካሄድ ፈፅሞ ተቀባይነት እንደሌለው አስታውቀዋል።

ችግርን ማባባስ ለሁሉም የሚበጅ መንገድ አይደለም ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ደመቀ መኮንን መንግሥት በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት በጥብቅ እንደሚወጣም አረጋግጠው፤ ለቤተክርስቲያኗ አንድነት ሁሉም አካላት አዎንታዊ ሚናቸውን እንዲወጡ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመከላከያ ሰራዊቱ እያከናወነ ያለው የአቅም ግንባታ የአንድነትና የሉአላዊነት መሰረት ነው!

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የጀግንነት መገለጫ ጥግ ነው፡፡ ሰራዊቱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የወጣ በመሆኑ ሁሌም ራሱን ለሕዝብና ለሀገር አሳልፎ ይሰጣል፤ የሀገሪቱን ሉአላዊነትን ለማስከበርና የዜጎችን ሰላም ለማረጋገጥ መስዋዕትነትን ይከፍላል፡፡ በዱር በገደሉ ይዋደቃል፡፡ ደሙን ያፈሳል፤ አጥንቱን ይከስክሳል፡፡

ኢትዮጵያውያን ከጥንት እስከ ዛሬ በደምና አጥንታቸው ታሪክ ሲሰሩ፤ ሀገር ሲያቆሙና ኢትዮጵያን ሲታደጉ ኖረዋል፡፡ ሀገሬን አላስደፍርም፤ማንነቴን አላዋርድም፤ ሰንደቄን አላስረግጥም በማለት በዱር በገደሉ ደማቸውን ሲያፈሱ፤ አጥንታቸውን ሲከስክሱ ኖረዋል፡፡ ዛሬም የዚሁ ውርስ የሆነው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በደምና አጥንቱ የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና አንድነት በማስከበር ታሪክ በመጻፍ ላይ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በጀግንነቱ ሁሉም በአንድ ድምጽ የሚስማማበት በሰላም ጊዜ የልማት አርበኛ ለድንገተኛ ክስተት የማይበገር ጀግና ሰራዊት ነው፡፡ ሰራዊቱ ድል የሚፈጥር፣ ሞትን የሚያሸንፍ፣ ለድንገተኛ ክስተት የማይበገር፣ ፍላጎቱን ለዓላማው የሚያስገዛ፣ የነፃነትን ዋጋ ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ የጨለማን ጊዜ ማሻገር የሚችል ልበ ሙሉ ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በሰላም ጊዜ የልማት አርበኛ በጦርነት ወቅት ጀግና ሆኖ በስኬት በመራመድ ላይ ይገኛል፡፡

የአንድ መከላከያ ሀይል እምቅ አቅምና ጥንካሬ፤ የመለኪያ መስፈርቶቹ፤ የሰራዊቱ ብቃትና የውጊያ ዝግጁነት የታጠቀው ዘመናዊ የጦር መሳሪያና በታጠቀውም መሳሪያ በየትኛውም የመሬት ገጽ ላይ ለመጠቀም ያለው ችሎታና ብቃት ሀገርን ለመከላከል በውስጥ በተለያዩ አውደ ውጊያዎች ተሰልፎ ያስመዘገበው ድልና ስኬት ከዚህም አልፎ

ድንበር ዘለል ተልእኮን በመወጣት ረገድ ያሳየው ወይንም የሚያሳየው ብቃት የአቅሙን ልኬት ሊያሳዩ የሚችሉ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የሀገሩን ዳር ድንበር ከማስከበሩም ባሻገር በጎረቤት ሀገራት ጭምር ተልዕኮ በመውሰድ ሰላምን በማረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡ በሶማሊያ፤ በሱዳን፤ ቀደም ሲልም በላይቤሪያ፤ በሩዋንዳና ቡሩንዲ ሀገራት ተሰማርቶ ሰላም ማስከበር የቻለ የሕዝብ ልጅ ነው፡፡ ይህም ብቃት ሊገኝ የቻለው ከሰራዊቱ ተፈጥሯዊ ባህሪ በሻገር በየጊዜው እየተደረገለት በመጣው አቅም ግንባታ ስራዎች አማካኝነት ነው፡፡

በተለይም ባለፉት አራት አመታት ሰራዊቱን ለማዘመን በተሰሩ የለውጥ ስራዎች የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወደ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋግሯል፡፡ ራሱን በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ በማጠናከር ሳይዋጋ የሚያሸንፍበት ብቃት ላይ ደርሷል፡፡

የምድር ኃይልን በሰው ኃይልና የውጊያ አፈጻጸም በማጎልበት ከአየር ኃይልና ከሌሎች አቅሞች ጋር ያለውን ቅንጅት የማሳደግ ዕድል ፈጥሯል፡፡ በትጥቅና በመረጃ ግንኙነት አቅሙን በመገንባትም የማሸነፍ ብቃቱን አሳድጓል፡፡ ከአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲና ከተለያዩ የደህንነትና የጸጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት የባህር ኃይልን አቅም የማሳደግና የሳይበር ጥቃት ዝግጁነት /የሳይበር ዋርፌር/ ብቃትን በማሳደግ ከተለመደው የውጊያ ስልት ወጣ በማለት የሚቃጡ ዘመን አመጣሽ ጥቃቶችን የመከላከል ብቃቶችን ተጎናጽፏል፡፡

መከላከያ ከለውጡ ወዲህ በሰራቸው የሪፎርም ስራዎች በቴክኖሎጂ አቅም ማሳደግ፣ በመከላከያ ምርምር ስራዎች፣ በባህር ኃይል ዝግጁነትና ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አከናውኗል፡፡ በሀገር ውስጥና በውጭ አገራት የተቃጡ ውስብስብ ጥቃቶችን የመመከት ብቃቶችን አዳብሯል፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ከሰላም ማስከበር ጎን ለጎን በልማት ስራዎች ላይ በመሳተፍ ለሀገሩ ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገነቡ ድልድዮችና መሰረተ ልማቶችን በመገንባት፤ የግብርና ምርቶችን በመሰብሰብ፤ የአርሶ አደሩን ምርቶች ከተባይና ከተፈጥሮ አደጋ በመጠበቅ የዜግነት ግዴታውን የሚወጣ የሕዝብ ልጅ ነው፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም የተፈናቀሉና ከቀያቸው የተሰደዱ ወገኖችን በመንከባከብና ካለው ላይ ለዕለት ጉርስ የሚሆን ገንዘብ በማዋጣትም ሕዝባዊነቱን የሚያሳይ ሰራዊት ነው፡፡

በአጠቃላይ ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ተቋም ላይ እየተሰሩ ያሉ የለውጥ ተግባራት የሰራዊቱን ሀገር የመከላከል አቅም የሚጨምርና የሀገሪቱን ሉአላዊነትና አንድነት የሚያስጠብቅ ነውና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ነው!

አዲስ ዘመን
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39
ማከፋፊያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# የአርሶ አደሩን የሥራ ባሕል የቀየረው የበጋ ግብርና

ኢያሱ መሰሰ

ኢትዮጵያ ድንበር ተሻጋሪ የሆኑና ያልሆኑ የበርካታ ወንዞች ባለቤት መሆኗን ተከትሎ የውሃ ማማ እየተባለች ብትወደስም ስሟና ግብሯ ሳይገናኙ ዘመናትን አሳልፋለች። አብዛኛዎቹ ወንዞቿ እንደዳቦ በሚገመጠው ለም መሬት መካከል ያለምንም ሥራ ሲገማሸሩ እና ሲተኙ የኖሩ በመሆናቸው አገሪቱ የወንዞቿን በረከት ለዘመናት ሳታጣጥም ኖራለች። አባይን ጨምሮ አንዳንዶቹ እንደውም ከለም አፈሯ እየዛቁ ወደ ጎረቤት አገራት ሲያግዙ የኖሩ በመሆናቸው ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ሚዛን ደፍቶ ነበር።

የአገራችን አርሶ አደሮችም ቢሆኑ በዝናብ ጥገኝነት ላይ የተመሰረተ የግብርና ሕይወትን ስለሚመሩ የመኸሩን አዝመራ ከሰበሰቡ በኋላ የበጋውን ወራት በወንዞች ተጠቅመው የማምረት ልምድ አልነበራቸውም። እንደውም ለአገራችን አርሶ አደሮች የበጋው ወራት እንደ እረፍት ጊዜ የሚቆጠር ነበር። በበጋ ወራት ወንዞች ለአርሶ አደሩ ይጠቅማሉ ከተባለ ምናልባትም ለከብቶች ውሃ መጠጫነት፣ ለንጽህና መጠበቂያነት እና ለመጠጥነት ቢሆን ነው።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ሁኔታዎች እየተለወጡ መጥተዋል። ይህ ዘመናትን ያስቆጠረው የወንዞቻችንና የመሬቶቻችን ተኳርፎ የመኖር ሁኔታ የስንዴ ፍላጎትን ለማሟላት በሚል ከተነቃቃው የበጋ ግብርና በኋላ መልኩን ቀይሯል። ዛሬ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች የመኸሩን አዝመራቸውን ከሰበሰቡ በኋላ እንደ ከዚህ ቀደሙ በበጋው ወራት እጃቸውን አጣጥፈው የሚቀመጡበት ሁኔታ የለም።

አርሶ አደሮቻችን የመንግሥትን አቅጣጫ ተከትለው ላለፉት ሶስት ዓመታት ወንዞችን እየጠለፉ የማልማት ባህላቸውን አሳድገዋል። ይህ አዲስ የሥራ ባህል ጅምር ላይ ባለበት በዚህ ወቅት ውስን ውሃ ገብ መሬቶችን ብቻ በማልማት አመርቂ ውጤት እንደተገኘ የግብርና ሚኒስቴር መረጃዎች ያመላክታሉ።

የበጋው ግብርና ገና በሚፈለገው ደረጃ ባልተስፋፋበት በዚህ አጭር ጊዜ ስንዴን ኤክስፖርት የማድረግ ቁመና ላይ ተደርሷል። ለበጋው ግብርና አመቺነት ያላቸው ወንዞቻችን እና መሬቶቻችን ሙሉ ለሙሉ ጥቅም ላይ ሲውሉ ደግሞ አሁን የተገኘውን ውጤት በሁለት እና በሶስት እጥፍ ማሳደግ እንደሚቻል መገመት አይከብድም። ልክ እንደ መኸሩ የምርት ዘመን ሁሉ የበጋውም ወራት መደበኛ የግብርና ሥራ የሚከናወንበት ይሆናል። ኢትዮጵያ በዓመት ሁለቴ የማምረት አቅም ታጎለብታለች። በምግብ ራሷን ከመቻል አልፋ ኤክስፖርት የማድረግ ህልሟንም እውን ታደርጋለች።

አዲሱ የሥራ ባህላችን በዝናብ ጥገኝነት ላይ ተቸንክሮ የኖረውን ኋላ ቀር ግብርና አሠራር ነጻ የሚያወጣም ጭምር ነው። የመኸሩ ወቅት አንዳንድ ጊዜ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ይፈተናል። የዝናብ እጥረት ፣ በረዶ፣ ዋግ፣ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ወዘተ በመኸሩ ግብርና ውጤታማነት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ አለ። ከዚህ አንጻር የመስኖ ግብርና የመኸሩን ወቅት ያህል ፈታኝ ሁኔታዎች አይገጥሙትም።

የመኸሩ ወቅት ግብርና ተፈጥሯዊ ችግሮች ሲያጋጥሙትና ምርታማነት ሲቀንስ የበጋው ግብርና የሚያካክስበት እድል ተፈጥሯል። ባለፉት ሶስት ዓመታት በበጋው ግብርና ከተገኘው በሚሊዮኖች ኩንታል የሚቆጠር የስንዴ ምርት ይልቅ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አርሶአደሮች አዲስ የሥራ ባሕል ማዳበራቸው በመጪው የግብርና ሥራ ላይ ተስፋ እንድንጥል ያደርጋል።

የውሃ ማማ ተብላ የምትወደሰው ኢትዮጵያ በ1966 ዓ.ም እና በ1977 ዓ.ም በድርቅ ስትመታ የሕዝቦቿ ብዛት ከ40 እስከ 70 ሚሊዮን እንደማይበልጥ የዚያን ዘመን መረጃዎች ያመላክታሉ። ያን ጊዜ በድርቅ ተመታን ብለን ለምጸዋት እጃችንን የዘረጋነው ከዛሬው የተሻለ አቅም ያላቸውና በለም መሬቶቻችን መካከል የተኙ ወንዞች እያሉን ነበር። የተከማቸውን የውሃ ሀብታችንን ልክ እንደ አሁኑ ለግብርና ሥራ ሳናውል ቀርተን በድርቅ የተመታንባቸው እና ምጽዋት የጠየቅንባቸው እነዚያ ዘመናት ሊያስቆጩን ይገባል።

አሁን መንግሥት ወንዞችን ተጠቅሞ ማምረት እንደሚቻል በተግባር እያሳየን ይገኛል። የአገራችን አርሶ አደሮችም አይናቸውን ገልጠዋል። እንደበፊቱ የዝናብ ጥገኛ ሆነው ክረምትን ለሥራ በጋን ለእረፍት ሳይሉ ክርምት ከበጋ እያረሱ ማምረትን ተለማምደዋል።

ውስን የውሃ ሀብት ያላቸው አንዳንድ የዓለማችን አገራት የመስኖ ግብርናን በማዘመን ሕዝባቸውን ከመመገብ አልፈው ለሌሎች አገራት የሚተርፍ ምርት ሲያመርቱ ስናይ ያለፈው የአገራችን የመሬትና የውሃ ብክነት ያስቆጨናል። እስራኤል በውስን መሬቷ ላይ የመስኖ ግብርናን በማስፋፋት ኢኮኖሚዋን የምትደጉም ተጠቃሽ አገር ነች። ጎረቤቶቻችን ሱዳን እና ግብጽም ከእኛው አገር የሚፈስላቸውን የአባይ ወንዝ ለመስኖ ሥራ በማዋል የተትረፈረፈ በረከት የሚያገኙ ምሳሌዎቻችን ናቸው።

ኢትዮጵያ እዚያው በዚያው መመጋገብ የሚችል የውሃና የመሬት ጸጋ የተቸራት አገር ሆኗ እስከዛሬ ድረስ በመስኖ ሥራ ስሟ አለመጠራቱ የሚያስገርም ነው። ከዚህ በኋላ ግን በየወንዙ ዳርቻ ተንጣለው የተቀመጡ ሰፋፊ መሬቶች ያለሥራ የሚቀመጡበት ዘመን ያለፈ ይመስላል። ወንዞቻችንም በራስጌ እና በግርጌያቸው በግራ እና በቀኛቸው ወደ ተንጣለሉት ለም መሬቶች እየፈሰሱ ምድሪቱን በልምላሜ የሚያፈኩበት፣ በረከታቸው ለአርሶ አደሩ የሚተርፍብት ዘመን ላይ ደርሰዋል።

እንደግብርና ሚኒስቴር መረጃ ያለፉትን የሶስት ዓመታት ልምድና ተሞክሮ በመቀመር በዘንድሮው የበጋ ወራት አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር በዘር ለመሸፈን ታቅዷል። የመኸሩ ምርት ከተሰበሰበ በኋላ ውሃ ገብ መሬት ያላቸው አርሶ አደሮች በሙሉ ወደ መስኖ ሥራ እንዲገቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሠርቷል።

መንግሥት የበጋ ግብርናን በማበረታታት ዓመታዊ የምርት መጠንን ከዓመት ወደ ዓመት እያሳደገ መምጣቱ አዲስ ለውጥ ነው። ይህን ልምድና ተሞክሮ በመላ አገሪቱ በማስፋፋት አርሶ አደሩን ከዝናብ ጥገኝነት አላቅቆ በግብርና ዘርፍ የታሰበው የእደገት ደረጃ ላይ ለመድረስ በእጅጉ የሚጠቅም ነውና ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

# ተጠየቅ

# “ሕዝብንም ሆነ አካባቢን ሊጎዳ የሚችል አንድም የግብርና ቴክኖሎጂ ወደ አገር ውስጥ አይገባም ”

**- ዶ/ር ታደሰ ዳባ**

**በግብርና ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ፕሮጀክት አስተባባሪ**

ግርማ መንግሥቴ

**ዛሬ ራዕዩን “ተፈላጊና የላቁ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ ውለው የዜጎች ሁለንተናዊ ህይወት በፍጹም ተለውጦ ማየት”ን ወዳደረገው፣ ነፍስን በሚያስመልም አፀድ በተዋበው፣ ሙሉ ፀጥታ ባረበበበትና መቀመጫውን ከመገናኛ ወደ ሃያት ሲያቀኑ መሀል ላይ ወደ ቀኝ ገባ ባለው ባደረገውና ከግማሽ ምእተ አመት በላይ በጥናትና መርምር የህይወት ሑደት ውስጥ ወደ ዘለቀው አገራዊ ተቋም አቅንተናል።**

**ይህ ግዙፍና አንጋፋ ተቋም በውስጡ በአገር ደረጃ የምርምር ስርዓቱ ውስጥ ለረጅም ዓመታት ያገለገሉ፣ ሙሉ የተመራማሪነት ማዕረግ የተሰጣቸው፣ የመሪ ተመራማሪነት ደረጃን የጨበጡ፣ ለአገራችን ግብርና ሳይንስ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ፣ የአገሪቷን የግብርና ዘርፍ በተለያዩ ችግር ፈቺ የግብርና ምርምር ቴክኖሎጂዎችና እውቀትን በማመንጨትና በማቅረብ ለአገራዊ ግብርና ምርትና ምርታማነት ማደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ፣ብእር ያልዳሰሳቸው፣ ሚዲያው ያልደረሰባቸው (ባጭሩ፣ ምንም ያልተዘመረላቸው) ተመራማሪዎች ይገኙበታል፡፡**

**የዚህ ተቋም የምርምር ፕሮጀክት አስተባባሪ ዶ/ር ታደሰ ዳባ ሲሆኑ በትህትና በታጀበና ጥኡም አንደበታቸው ስለ ተቋሙ፣ በተለይም ስለ ግብርና ቴክኖሎጂ አጠቃላይ ሁኔታና ይዞታ እንደሚከተለው አውግተናል።**



ፎቶ-ሐዱሽ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፡- ይህ መድረክ መቼ ተቋቋመ እና አላማው ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** የግብርና ባዮቴክኖሎጂ ከሌሎቹ አኳያ ሲታይ አዲስና ከግብርና ሳይንሶች ሁሉ ረቀቅ ያለ ሳይንስ እንደ መሆኑ መጠን፣ እሱን ለማጥራት፣ ግልፅ ለማድረግና ለህብረተሰቡ ለማስረዳት፤ ከዛም ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ፤ የአካባቢያዊ ችግሮችን ስጋት ለመቀነስ ወዘተ ሲባል የተቋቋመ ነው፡፡

በአፍሪካ ደረጃ ኬንያ ላይ በ2006 ነው የተቋቋመው። ተግባሩም በአህጉር ደረጃ በግብርና ዙሪያ ማስተባበር ነው። ያኔ፣ ይህ ፎረም ሲቋቋም የአፍሪካ አገራት ስምንት ነበርን። አሁን አስር ደርሰናል።

ተቋሙ በአገራችን እንደ አንድ ወሳኝ የምክክር መድረክ ታስቦ፣ በ2006 የተቋቋመው አፍሪካ አቀፍ ፎረም አባል ሆኖ የተቋቋመው በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2014 ነው። ሲቋቋምም ዋና አላማው እርስ በርሳቸው የማይተዋወቁ በርካታ የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን የተቋቋሙ፤ እርስ በእርሳቸው ባለመናበባቸው ምክንያት በተፈለገው መጠን ውጤታማ ሊሆኑ ያልቻሉትን፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና አለም አቀፍ ተቋማትን (ግብረ ሰናዮቹን ጨምሮ) እና ሌሎችንም በማሰባሰብ ተናበው፣ ተመጋግበው . . . እንዲሰሩ፤ በጋራ ጥረት የጋራ ተጠቃሚ እንዲሆኑና የግብርናውን ዘርፍ የበለጠ በማዘመን በኩል ተገቢውን ድርሻ እንዲወጡ . . . በማሰብ ነው።

ግንኙነታቸው በጣም የላላ የነበሩትን፤ የሙያተኞች ትስስር (ፕሮፌሽናል ኔትዎርክ) መፍጠርና ምሁራን፣ ባለሙያዎች፣ ባለድርሻ አካላት . . . እየተገናኙ ለጋራ ጥቅም የሚመክሩበት መድረክ መፍጠርም ሌላው ታሳቢ ተደርጎ የነበረ ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ ከአገርም አልፎ አህጉርንም ተሻግሮ አለም አቀፍ ይዘት ያለው በመሆኑ የተቋሙን መቋቋም አስፈላጊነት ተገቢ ያደርገዋል።

በአገር ውስጥ ለተገኙ ውጤቶችና ስኬቶች ተገቢ ማሳያ የሚሆነው ጥጥ ምርትን በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠቃው “ቦልዎርም” የተሰኘ ህዋስ ጥጡን እንዳያጠቃ ማድረግ መቻሉ ሲሆን በሌሎች ምርቶችም በተመሳሳይ የተሰሩ ስራዎች አሉ

ይህ ብቻም አይደለም፣ አንድ ምርት ልውጠ ህያው ምርምር ተካሂዶበት አዋጭነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ወደ ተግባር ከመግባቱ በፊት በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ እንደማያሳድር በሳይንሳዊ ምርምር የማረጋገጡ ስራ የዚሁ ተቋም ኃላፊነት ነው።

ኬንያ ውስጥ ከላይ በቁጥር በጠቀስናቸው የአፍሪካ አገራት ከተቋቋመው (Open Forum on Agricultural Bio-technology (OFAB)) ፎረም በመነሳት የኢትዮጵያም “OFAB-Ethiopia” በሚል ስያሜ ተመሰረተ። በአዲስ ሳይንስ አራማጅ፣ አስተዋዋቂነቱ (“Agricultural Bio-technology”ን ማለት ነው) እውቅናን አገኘ።

ሌላው የተቋቋመበት አላማ ምርቶች በትክክል ተደራሽ እንዲሆኑና በሚገባ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ሲሆን፣ በዚህ በኩልም በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል።

በአሁኑ ሰአት በመንግሥትና የግል ተቋማት፣ በዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎች አካባቢዎች የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። ተቋሙ (የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት) የግብርና ባዮ-ቴክኖሎጂን ስለ መጠቀም፣ በተለይ ለሰብልና ለእንስሳት ምርምር ውጤታማነት ያለውን አስተዋጽኦ፣ ዘረመላቸው የተለወጡ የሰብል ዝርያዎች በኢትየጵያና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉበትን ሁኔታና እያበረከቱ ያሉትን ድርሻ ... የመሳሰሉትን ተገቢ መሆን/አለመሆንን የመለየት ስራን ያካተተ ነው።

በዚህ አጋጣሚ የልውጠ ህያው ስራ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ብቻ ተብሎ የሚሰራ አይደለም። ጤናን ከመጠበቅ አንፃር፣ አካባቢን ከመንከባከብ፤ በሽታን፣ የአየር ጠባይን ከመቋቋም ወዘተርፈ አኳያ ሁሉ ነው ታስቦ፣ ታቅዶና ታልሞ የሚሰራ ነው። ይህ ማለት ደግሞ፣ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ሰብሉን የመቀየር ስራ አይደለም። ሰብሉ የጎደለውን ማሟላት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እና ይህ፣ በጋራ የመምከሩ፤ የመግባባቱ ወይም ውጤት ላይ የመድረሱ ጉዳይ ተሳክቶላችኋል?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** አዎ፣ እየተሳካልን ነው። በርካታ ተበታትነው ይሰሩ የነበሩ ዘርፎችን በማሰባሰብና ተናብበው እንዲሰሩ በማድረግ ጥሩ ጥሩ ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን። ባለ ድርሻ አካላትንም እያሳተፍን ስለ ሆነ ጥሩ እየሄደ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋማችሁ (ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት) በአብዛኛው በተመራማሪዎች የተሞላ ነው። ከተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋርም አብራችሁ ትሰራላችሁ። በተለይም አለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ልምድን ያካበቱ ኢትዮጵያዊያን ይበዛሉ። ከዚህ አኳያ የምርምር ስራችሁ ለኢትዮጵያ አርሶ አደርም ሆነ ለሴላው (እንደ አገር) ምን አስገኘ?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** እውነት ነው። ይህ የምርምር ተቋም፣ ወይም የግብርና ምርምር ስራ በአገራችን ከ60 አመት በላይ እድሜ አለው። በእነዚህ አመታት ሁሉ የምርምር ስራን ሲያከናውን ነው የቆየው። በርካታ ውጤቶችንም አምጥቷል።

እንደ አገር ከፍተኛ የምርምር ስራዎች የሚሰሩበት ተቋም እንደ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አለ ለማለት ያስቸግራል። በግብርና ምርምር ተቋሟት ነው በርካታ የምርምር ስራዎች የሚካሄዱት።

ለምሳሌ በጤና፣ ኒውትሪሽን (ስነምግብ) እና የመሳሰሉት ላይ የሰራናቸው በርካታ ስራዎች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህና የመሳሰሉት ሁሉ በተጠቃሚው ዘንድ በአይን የማይታዩ ናቸው። ተመራማሪዎቻቸውንም እንደዚሁ ብዙም ልብ የሚላቸው የለም። ነገር ግን ከጀርባ ያሉት ትልልቅ ስራዎች ትልቁንና ውስብስቡን ስራ እየሰሩ ለህዝብ ያደርሳሉ። ልክ እንደ እነዚህ ሁሉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። እየተሰሩም ይገኛሉ።

በጥቅሉ እንጥቀሰው ብንል እንኳን፣ የግብርናውን ዘርፍ ሊያሻሽሉ የሚችሉ በአገር ደረጃ ከ1ሺህ 140 በላይ የምርምር ስራዎች ተለቅቀዋል። ቤተ ሙከራ ገብቶ መመልከት እንደሚቻለውም፣ እስከ ዛሬ የተሰሩና እየተሰሩ ያሉት ስራዎች ብዛት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ወደ ተግባር ተቀይረው ውጤት ያስገኙ ናቸው። ምናልባት ይሄ ካለን የአገራችን የቆዳ ስፋትና መሰል ጉዳዮች አኳያ በቂ ነው/አይደለም የሚለው ካልሆነ በስተቀር በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ዘረ መል ልውጥ አካል ወቅታዊ አለም አቀፍ ይዞታው ምን ይመስላል?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** በአለም አቀፍ ደረጃ ያለው እውነታ እንደሚያሳው ባዮቴክኖሎጂ ከፍተኛ ለውጥ እያመጣና ምርትና ምርታማነትን እያሻሻለ ይገኛል። ለምሳሌ አርጀንቲና፣ ብራዚል፣ ኡራጓይ፣ ጃፓን . . . ወዘተ የመሳሰሉ አገራት በዚህ ዘርፍ ተጠቃሚ ሆነዋል። የቴክኖሎጂው ባለቤት የምትባለው አሜሪካም እንደዛው። ሌሎችም አሉ። አፍሪካም በዚሁ መንገድ እየሄደች ትገኛለች።

**አዲስ ዘመን፡- በአገር ውስጥስ? ያስገኘው ውጤት ካለ ማለት ነው።**

**ዶ/ር ታደሰ፡-**እርግጥ ነው፤ ይህ ቴክኖሎጂ እድሜው 35 አመት አካባቢ ይሁን እንጂ ወደ አፍሪካ የገባው በቅርቡ ነው። በተለይም ወደ እኛ አገር የገባው በጣም በቅርቡ ነው። በመሆኑም አስቀድመው ቴክኖሎጂውን ከተቀበሉትና ወደ ተግባር ከገቡት አገራት እኩል ለውጥ አምጥተናል፤ ወይም፣ ውጤት አስመዝግበናል ማለት አይደለም። ያም ሆኖ ከማለማመድና መፈተሽ ጀምሮ ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል።

በዘረመል ምሕድስና (ልውጠ ህያው) ትኩረት ተሰጥቶ የማይሰራባቸው ምርት ሰጪ ጉዳዮች አሉ ማለት ባይቻልም፣ ልውጠ ህያው ምርምር ተካሂዶበት ወደ ምርት ከገባው ጥጥ ምርት ጀምሮ በበቆሎ፣ እንሰት፣ ድንች . . . ዝርያዎች ላይ የልውጠ ህያው ምርምር ሲካሄድ ቆይቷል። የምርምር ስራ የሚቆምና እዚህ ጋ በቃ የሚባል ባለመሆኑ ስራው ያለ ማቋረጥ እየተካሄደም ነው።

ሌላው በአገር ውስጥ ለተገኙ ውጤቶችና ስኬቶች ተገቢ ማሳያ የሚሆነው ጥጥ ምርትን በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠቃው “ቦልዎርም” የተሰኘ ህዋስ ጥጡን እንዳያጠቃ ማድረግ መቻሉ ሲሆን በሌሎች ምርቶችም በተመሳሳይ የተሰሩ ስራዎች አሉ።

በእስከ ዛሬው አሰራር የቅድመ ምርምርና ጥናት እንዲካሄድ ፈቃድ የተሰጣቸውና ወደ ተግባር የተገባባቸው እንዳሉ ሁሉ ወደ ፊትም በዚሁ አሰራር መሰረት በዘረመል ምሕንድስና (ልውጠ ህያው) ላይ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል። የግብርናውን ዘርፍ የማዘመኑ ጉዳይም በዛው ልክ ይካሄዳል ማለት ነው። የ“ክፍት ምክክር መድረክ ፕሮጀክት” (OFAB-Ethiopia) ሂደቱም ሌላው ማሳያ ነው።

በአገር ውስጥ ፕሮጀክቱ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ለመሆኑ ማሳያው ሳይንሱ እንደ አንድ ራሱን የቻለ ጥናት መስክ በተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ መሰጠቱ፤ በአንዳንድ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ጥናቶች ብቻ ይነካካ የነበረው ዛሬ በስፋት እየተጠና መሆኑ፤ የተለያዩ ተቋማት፣ ለምሳሌ ዩኒቨርሲቲዎችና አካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሰሩ፤ በግብርናው መስክ የተሰማሩ እና ሌሎችም ድሮ ለየብቻቸው ይንቀሳቀሱ የነበረው ቀርቶ አሁን በጋራ መስራታቸውና መናበብ መቻላቸው ነው። ይህ ደግሞ

# ተጠየቅ



> ለእኛ አዲስ ይሁን እንጂ ሌሎች አገራት ወደ ተግባር ቀይረውት ተጠቃሚ በመሆን ላይ ናቸው። በመሆኑም ህብረተሰባችን፣ ይሄ የሚነዛውን፣ ምንም አይነት ሳይንሳዊ መሰረት የሌለውን የሀሰት ትርክት ወደዛ ትቶ የዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆን አለበት

በዚሁ ዘርፍ ከፍተኛ ውጤትና ተጠቃሚነትን እያስገኘ ይገኛልና ፕሮጀክቱ በአገር ውስጥም በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው። እየተካሄደ ነው ማለት ብቻም ሳይሆን ተቋማዊ ይዘት ባለው መልኩ እየተሰራ ይገኛል።

እንሰትን በተመለከተ ያለውን ችግር ለመቋቋም የሚያስችል ሰፊ ሥራ ተሰርቶ (ለምሳሌ በኡጋንዳ) ጥሩ ውጤት እንደ ተገኘው ሁሉ፣ በእንሰት ላይ በተለይ በደቡባዊ ኢትዮጵያ የኮባ ቅጠልን በማጠውለግ የሚያደርቀውን በሽታ የሚቋቋም የልውጠ ህያው የእንሰት ዝርያ ለማውጣት እየተሰራ ይገኛል። ሌሎችም በርካታ ስራዎችም እየተሰሩ ይገኛሉ። እነዚህ ሁሉ፣ ሳይንሱ ወደ አገራችን በቅርቡ የገባ ከመሆኑ አኳያ፣ የሚያበረታቱ ስራዎች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ዘረመል ልውጥ አካል ((“ልውጠ ህያው“ በሚል የሚገለፁትም አሉ) (GMOs)) ሲባል ምን ማለት እንደ ሆነ አውዳዊ በሆነ መልኩ ቢገልፁልን?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** በመጀመሪያ ”ልውጠ ህያው” የሚለው ራሱ ወደ አማርኛ ሲመለስ ችግር አለበትና ወደ ፊት ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ሙሉ ለሙሉ ጽንሰ ሀሳቡን በሚገልጽ ደረጃ አይደለም የተተረጎመው። ለዚህ ችግር ዋናው ምክንያቱ ደግሞ ፅንሰ-ሀሳቡ በአለም አቀፍ ደረጃ በጣም ሰፊና በርካታ ጉዳዮችን ያካተተ በመሆኑ ነው።

በአሁኑ ሰአት ይህ ”ልውጠ ህያው” የሚባለው በብዙ አገራት የመወያያ ርእሰ ጉዳይ እየሆነ ይገኛል። ምክንያቱ ደግሞ ይህ የዛሬ 35 አመት አካባቢ ገበያ ላይ በዋለው ጄኔቲክ ኢንጂነሪንግ የሚሰራ፣ በጣም ረቂቅና ከባድ የሆነው “ጄኔቲክ ሞዲፊኬሽን” (ልውጠ ህያው) አዝርእት ወይም እፅዋት ባህሪያቸውን እንዲለውጡ ታስቦ የሚሰራ ስራ (የጥናትና ምርምር መስክ) ነው።

**አዲስ ዘመን፡-** እንደምንሰማውም፣ እንደምናነበውም ከሆነ “ፀረ ዘረመል ምሕንድስና አቀንቃኞች” የሚባሉ፣ ከእናንተ የተለየ (ተቃራኒ የሆነ) አቋም ያላቸው ወገኖች አሉ። ማን ነው ትክክል፤ እናንተ ወይስ እነሱ?

**ዶ/ር ታደሰ፡-** ተቃውሞ በሁለት ጉዳዮች ሊመጣ ይችላል። አንዱ ከስጋትና ፍርሀት፣ ቴክኖሎጂውን ከመጠራጠር ... የሚመጣውና ጤናኛው ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ ከጀርባው ትልልቅ ኩባንያዎች ያሉበት ተቃዋሚነት ነው።

እንዳልከው፣ አዎ፤ እነዚህ አቀንቃኞች አሉ። ይኑሩ እንጂ ሁሉም ከጥቅም በስተቀር ምክንያት የለሾች ሲሆኑ፤ ከፍተኛ ገንዘብ ተከፋዮችም ናቸው። በተለይም በልውጠ ህያዋን መስክ የሚታየው ፅንፈኝነት ከግል ጥቅም የሚመነጭ መነሻ ነው ያለው። ከእነዚህ ወገኖች ጀርባ እነሱ “ኦርጋኒክ” (በመሰረቱ “ኦርጋኒክ” የሚባል ነገር የለም) የሚሉት ምርት አምራች፣ አከፋፋይ ... የሆኑ ቱጃር ኩባንያዎች አሉ። እነዚህ ወገኖች የእነሱ ምርት እንዲሸጡላቸው ይሄንን ያጣጥላሉ። ለዚህ ደግሞ እነዚህን፣ በምንም አይነት ሳይንሳዊ መሰረትና መረጃ ላይ ያልቆሙ፣ ሊቆሙም የማይችሉ “በሳይንሳዊ እውነታዎች ላይ መከራከርን የማይደፍሩ፤ እውነታውን እያወቁ እንዳላወቀ የሚክዱ ወገኖችን ያሰማራሉ። በቃ፣ እውነታው ይሄው ነው።

እኛ የምንፈልገው ሰዎች ይሄንን አጥርተው እንዲያውቁ ነው። ይህንን፣ በገንዘብ የሚሾር ፖለቲካል ኢኮኖሚ አቀንቃኝነትን በውል ለይቶ መታገል ይገባል። ይህንን በምሳሌ ማየት ይቻላል። ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም መድሀኒቶች የሚመረቱት አውሮፓ ነው። ገበያቸው ያለው ደግሞ አፍሪካ ነው። በመሆኑም አፍሪካ ያንን መድሀኒት ማምረት ቻለች ማለት የእነሱ ገበያ ተዘጋ ማለት ነውና ያ እንዳይሆን በከፍተኛ ደረጃ የሀሰት ትርክት የመንዛትና በምንም አይነት መሰረት ላይ ያልቆመን ፕሮፓጋንዳ የመርጨት ሁኔታ ይኖራል። ይህንን ነው እኛ በውል ልገነዘበው የሚገባን ማለት ነው። ባጭሩ፣ በባዮቴክኖሎጂ (ልውጠ ህያው) አማካኝነት ለውጤት የሚበቁ ምርቶች ምንም አይነት ችግሮች የሉባቸውም።

አንድ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ቢኖር አንድ አዝርእት ከ40 እስከ 48ሺህ ቅንጣት ዘረመል (ዲኤንኤ) ያለው መሆኑና በዚህ ምህንድስና አማካኝነት የሚሰራው ስራ ከእነዚህ ውስጥ አንዷን ለይቶ የማጎልበት ስራ እንጂ ሙሉ ለሙሉ የመለወጥ ስራ የማይሰራ መሆኑን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኦርጋኒክ ስለሆነና ስልሆነው ትንሽ ቢነግሩን?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** በመሰረቱ ይሄ “ኦርጋኒክ” የሚሉት ነገር ውሸት ነው። “ኦርጋኒክ ነው” እያሉ የሚነግሩንም ሆነ በየሱፐር ማርኬቱ የሚሸጡልን የውሸት ነው። “ኦርጋኒክ” ማለት ምንም አይነት ፀረ-አረምም ሆነ ፀረ-ተባይ ወይም ማዳበሪያ፣ ማለትም ማንኛውንም ሳይንሳዊ ድጋፍም ሆነ ተጨማሪ ማበልፀጊያ ያልነካውና ሙሉ ለሙሉ በተፈጥሮ ብቻ የዳበረ ማለት ነው። ያ ደግሞ እጅግ ሲበዛ ውሱን ነው። ያለው ምርት ቢያንስ ፀረ-አረም፣ ፀረ-ተባይ፣ ማዳበሪያ ወዘተ የነካው ነው። ይህ ደግሞ ”ልውጠ ህያው” አይደለም፤ ኦርካኒክም አይደለም። በዚህ መታለል የለብንም። “ኦርጋኒክ ነው” የሚሉን የውሸት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ነባሩን፣ ተፈጥሯዊውን ከማቆየትና እንዳይጠፋ ከማድረግ አኳያ እየተሰራ ያለ ስራ ካለ? ይህ የብዙዎች ስጋት እንደ መሆኑ መጠን በተጨባጭ ቢያስረዱን።**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** ጥሩ ጥያቄ ነው። የብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ዋና ስራው ይሄ ነው። ማቆየት፣ መለየት፣ ሲያስፈልግ ለስራ ማቅረብ። ይህ ማለት ግን የሱ ስራ ብቻ ነው ማለት አይደለም። እኛም የምንሰራው አለ።

ከሁሉም በፊት ግን የሚጠፋ ነገር አለመኖሩን መረዳት ያስፈልጋል። የመቀየር ነገር ከሆን አዝርእት ራሳቸውን ከተለያዩ ለውጦች ጋር (ለምሳሌ፣ የአየር ለውጥ) ለማዋሃድ፣ አብሮ ለመሄድ፣ ለመቋቋም ... ሲሉ ራሳቸውን በሂደት ይቀይራሉ። ባለበት የሚቆይ ነገር የለም። ልክ እንደ ቫይረስ ሁሉ ራሳቸውን ከሁኔታዎች ጋር ለማጣጣም ሲሉ እየተለወጡ ሊሄዱ ይችላሉ። ለምሳሌ እኛ በበቆሎ ምርት ከአፍሪካ አንደኛ ነን። ይህን ስናመርት አንድም የበቆሎ ዘር ከውጭ አምጥተን ዘርተን አናውቅም። ሎሚ ላልከው እስከ ዛሬ ሎሚን ያሻሻለ አገር በአለም የለም። የተሻሻለ የማንጎ ዝርያም እንዲሁ ነው፤ በአንድም አገር በባዮቴክኖሎጂ የተሻሻለ የማንጎ ዝርያ የለም። በመሆኑም ስጋቱ ተገቢ ሲሆን፣ ችግሩ ግን የለም። አይፈጠርም። ማለትም፣ በባዮቴክኖሎጂ ሳይንስ ትግበራ ምክንያት ነባሩ አይጠፋም።

**አዲስ ዘመን፡- የግብርና ባዮቴክኖሎጂን መጠቀም ግዴታ ነው?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** አዎ፣ ግዴታ የሚሆንባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። ለምሳሌ የአፈር መከምጠጥን በምን ትከላከለዋለህ? እሱ ብቻም አይደለም፤ በበቆሎ ምርት አንደኛ ነን እንላለን፤ በቆሎን የሚያጠቃውን ተምች በሽታ መከላከል ካልተቻለ አንደኛነቱ ከየት ይመጣል? ምርቱስ ቢሆን? ተምችን መከላከል የሚቻለው ደግሞ የባዮቴክኖሎጂ ሳይንስን ስራ ላይ በማዋል ነው፤ የጥጥንም ጉዳዩ ከዚሁ ጋር አንስቶ በተጓዳኝ ማየት ይቻላል። ባጠቃላይ፣ ከላይ እንዳልነው፣ ልውጠ ህያውን ስራ ላይ የምናውለው ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ብቻ አይደለም። ለእነዚህ፣ እዚህ ለጠቀስናቸውና ለሌሎች በርካታ ጉዳዮች መፍትሄ ለመሻት ሲባልም ጭምር ነው። በዚህ ላይ በደንብ አድርጎ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ባለ ድርሻ አካላት አሏችሁ?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** አዎ (ሳቅ)፣ ምግብ የሚመገብ በሙሉ ባለ ድርሻ አካላችን ነው። ከተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (አሁን ስድስት ሲሆኑ እየጨመረ የሚሄድ ነው) ጋር አብረን እየሰራን ነው። አርሶ አደሩ ባለድርሻ አካላት ባለ ድርሻዎቻችን ናቸው። መሰል የጥናትና ምርምር ተቋማትና ሚዲያውም እንደዛው።

በተለይ ለህዝቡ፣ በተለይም እታች ላለው አርሶ አደር ተደራሽ ከመሆን አኳያ ትልቁ ባለ ድርሻ አካሎቻችን የመገናኛ ብዙሀን ተቋማት ሲሆኑ፤ በቅርብ አብረን እየሰራን ሲሆን ወደፊትም ግብርናው ላይ በማተኮር የበለጠ እንሰራለን ብለን እናስባለን። በተለይ መረጃዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመተንተን፣ ለህዝብ ተደራሽ በማድረግና እውነታውን ከማስረዳት፣ የሀሰት ፕሮፓጋንዳውን ከማክሸፍ አንፃር የመገናኛ ብዙሀን ድርሻ የማይተካ ነውና እንደ አንድ ባለድርሻ አካል ያግዙናል ብለን እናስባለን። በአሉ አሉ ... ብቻ ሳይሆን መረጃን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማብራራት በህብረተሰቡ ዘንድ ተገቢው ግንዛቤ ይኖር ዘንድ በመስራት ከጎናችን ይሆናሉ ብለን ነው ከእነሱ ጋር አብረን እየሰራን ያለነው። በተለይ እዚህ አገር በትላልቅና ታዋቂ በሚባሉት ምሁራኑ ዘንድ ሳይቀር ብዥታ ስለሚታይ ያንን ብዥታ ከማስወገድ አንፃር ትልቅ አቅም ያላቸው የመገናኛ ብዙሀን በመሆናቸው በሚገባ ያግዙናል የሚል እምነት አለን።

**አዲስ ዘመን፡- ዘርፉ የመንግስት ፖሲሲ አለው። ይታወቃል?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** አለው። መታወቁን በተመለከተ አሰራጭተናል። መገናኛ ብዙሀን እጅም እንዲገባ አድርገናል። የበለጠ እንዲታወቅ ከማድረግ አኳያም እየተሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ወደ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንምጣ። አዳዲስ ምሩቃንን ትቀበላላችሁ? ማለትም ”እንድንማር ግፌት ተደርጎብን ከተመረቅን በኋላ ግን የሚቀጥረን አጣን‘ የሚል የምሩቃን ቅሬታ ስላለ ነው። ምናልባት ይሄ እርሶን የማይመለከት ከሆነ ልናልፈው እንችላለን።**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** ጉዳዩ የሂዩማን ሪሶርስ ጉዳይ ስለ ሆነ ዞሮ ዞሮ ይመለከተናል። እዚህ ላይ ጉዳዩ እንደ አገር ነው መታየት ያለበት። በእኛ አገር ትልቁ ቀጣሪ መንግስት ነው። ባደጉት አገራት ደግሞ የግሉ ዘርፍ ነው። በመሆኑም፣ እዚህ ያለው የሰው ሀይልን የማሟላት ጉዳይ፣ እንደማንኛውም መስሪያ ቤት ሁሉ፣ በቀጥታ ከመንግስት በጀትና እቅድ ጋር የተያያዘ ነው። በመሆኑም፣ በጀት ሲኖር የሰው ሀይል ቅጥር ይካሄዳል። በጀት ከሌለ ቅጥሩ አይካሄድም። ለዚህ ነው፣ እኛም በየሁለት አመቱ እናካሂድ የነበረውን ቅጥር ለጊዜው ያቆምነው። በጀቱ ሲኖር እንቀጥላለን ማለት ነው። ያ ነው እንጂ ሙያውና ሙያተኞቹ በጣም አስፈላጊዎቻችን ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ቀረ የሚሉት ካለ?**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** ይህ ቴክኖሎጂ ለአገራችን አዲስ ቴክኖሎጂ ነው። ለእኛ አዲስ ይሁን እንጂ ሌሎች አገራት ወደ ተግባር ቀይረውት ተጠቃሚ በመሆን ላይ ናቸው። በመሆኑም ህብረተሰባችን፣ ይሄ የሚነዛውን፣ ምንም አይነት ሳይንሳዊ መሰረት የሌለውን የሀሰት ትርክት ወደዛ ትቶ የዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆን አለበት። ዘርፉን የምናበለፅገው ኢትዮጵያዊያን ነን። እዚህ ያለነውና ዘርፉን የምንመራውም ሆንን፤ ሳይንቲስቶቻችንና ምሁራኖቻችን ፍፁም ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ ወገናቸውን የማገልገል ከፍተኛ ፍላጎትና ግዴታም ያለባቸው ... ናቸው። ማንም የተለየ አላማና ፍላጎት የለውም። ሁሉም ወገን አለው። ሁሉም በአገራዊ ኃላፊነት ነው የሚሰራው። ህዝብንም ሆነ አካባቢን ሊጎዳ የሚችል አንድም የግብርና ቴክኖሎጂ ወደ አገር ውስጥ አይገባም። በሳይንስ ያልተረጋገጠ አንድም ነገር ስራ ላይ አይውልም። ወደ ህብረተሰቡ እንዲሄዱ የሚደረጉት ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ደህንነታቸው የተረጋገጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነውና ህብረተሰቡ የግብርና ቴክኖሎጂ ምርቶችን ያለ ምንም መጠራጠር ሊጠቀም ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለ ሰጡኝ ሙያዊ ማብራሪያ አመሰግናለሁ።**

**ዶ/ር ታደሰ፡-** ለግብርና ባዮቴክኖሎጂው ዘርፍ ትኩረት ሰጥታችሁ እዚህ ድረስ መጥታችሁ ሃሳቤን እንድገልፅ እድል ስለሰጣችሁኝ እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## ሀገሬን የሚፈውሱ ልባም ልቦች

**ኢትዮጵያ** ታማለች፤ ያውም ልቧን:: መፍትሔዋ የሚመጣው በጤነኛ ልብ የሚመሩን፣ የሚያገለግሉን፣ በፈረሰው በኩል ቅጥሯን ለመድፈን የሚታትሩ ዜጎች ሲበረክቱ ነው

### ልብን የታደገ መልካም ልብ፤

ታሪኩን ያደመጡ የዓለም ሕዝቦችን በሙሉ በእምባ ያራጨ አንድ እውነተኛ ታሪክ በማስታወስ ልንደርደር:: ይህንን ታሪክ ያሰራጨው MBC4 Channel የተባለው ታዋቂ የቴሌቪዥን ጣቢያ ነበር:: ሐምሌ 10 ቀን 2003 ዓ.ም ከምሽቱ አንድ ሰዓት ግድም ትልቅ ዝና ባተረፈችው በኦፕራ ዊንፍሬ ሾው ላይ የተላለፈው ይህ ታሪክ እንደ አዘቦት ቀን ዝግጅቷ ታዳሚዎቿ እየሳቁ የተፍነከነኩበትና ያጨበጭቡበት ታሪክ አልነበረም:: ታዳሚው በሙሉ የተከታተለው ሲቃ እየተናነቀው እንደነበር እድል ገጥሟቸው ያዩት ያስታውሱታል::

“የቺካጎ ቢርስ” (Chicago Bears) ዝነኛ የቅርጫት ኳስ ተጫዋች የሆነው የቻርለስ ቲልማን ጨቅላ ሕጻን ቲያና ቲልማን በተወለደች በ6 ወር እድሜዋ በከባድ የልብ ሕመም መሰቃየት ትጀምራለች:: ይህንን የልጃቸውን ጭንቀት ያስተዋሉት ዝነኛው የቅርጫት ኳስ ጠቢብ አባቷ እና እናቷ ጃኪ በቤታቸው የሞት ጥላ አጥልቶ ስለነበር ትኩረታቸው ሁሉ በሕጻን ልጃቸው ላይ ነበር::

የልጃቸው ሕመም ቅስማቸውን የሰበረው አባትና እናት እንባቸውን የእለት ቀለባቸው አድርገውና በራቸውን ዘግተው እህህ እያሉ በሚቃትቱበት በዚያ ክፉ ወቅት ወሬ አነፍናፊዎቹ የሚዲያ ሪፖርተሮች ዝነኛው ኮከብ ስፖርተኛ ስለምን ሊሰውር እንደቻለ ፍንጭ ስላጡ “ቲልማን ሆይ! ወዴት ተሰወርክ? ተወዳጁ የቅርጫት ኳስ ስፖርት በቲልማን መጥፋት ምክንያት ጦም ውሎ ጦም አደረ! ቲልማን ሆይ ድምጽህን አሰማ!?” እያሉ በቤቱ አካባቢ ማንዣበብን ልማድ አድርገው ሰነበቱ::

ይህ ጉዳይ እጅግ ያስጨነቀው ቲልማን ከስፖርቱ ሜዳ ለምን ሊርቅ እንደቻለ እየጎተጎቱ ፋታ ከነሱት አስጨናቂ የሚዲያ ባለሙያዎች መገላገሉን ስለፈለገ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚዲያ ፊት ቀርቦ ስለ ታማሚዋ ልጁ ሕዝቡና አድናቂዎቹ እንዲጸልዩለት በመማጸን በቅርብ ጊዜ ወደሚወደው ስፖርት እንደሚመለስ አጭር መግለጫ ሰጠ::

በዚያው ተመሳሳይ ወቅት በሚኒሶታ ስቴት በሚገኝ አንድ የልጆች ሆስፒታል ውስጥ አማንዶ የሚባል የዘጠኝ ወር ሕጻን በልብ ሕመም እየተሰቃየ በጽኑ ሕሙማን ዋርድ ውስጥ በከፍተኛ ሕክምና ላይ ነበር:: ካለ አባት ልጇን ከምታሳድገው እናቱና ከአንድ ሴት ልጇ በስተቀር ተንከባካቢ ያልነበረው ይህ ሕጻን ሕክምናው ሳያሳካለት ቀርቶ ዜና እረፍቱ የተሰማው የቲያና አባት የልጁን ሕመም በሚዲያ በገለጸበት ሰሞን ነበር::

የቲልማን የጸሎት ተማጽኖና የልጁ ሕመም ከጆሯቸው የደረሰው ሐኪሞች በሕጻኑ ሞት ምክንያት ማዘናቸው ባይቀርም ለእናቱ አንድ ጥያቄ አቀረቡላት:: “እባክሽ የሟች ልጅሽን ልብ በልብ ሕመም እየተሰቃየች ላለችው ለቺካጎዋ ሕጻን ለቲያና ቲልማን እንዲሰጥ ፍቀጅልን?” የሟች እናት አላመነታችም:: የሞቷን ቀን ለምትጠባበቀው ለጭቅላዋ ቲያና የልጇ ልብ እንዲሰጥ ተስማምታ ፈረመች::

የሚኒሶታ ሐኪሞችም የአማንዶን ልብ ለቲያና ለማድረስ ዝግጅታቸውን አጠናቀው በግል ቻርተር አውሮፕላን ሊንቀሳቀሱ ሲሉ ወቅቱ ክረምት ስለነበር “መላ ቢሱ” የሚኒሶታ ክፍለ ግዛት በረዶ “ሰማዩን ቀዶ” ቁልቁል መንዥቅዠቅ ጀመረ:: ይህ ጸሐፊ ክፍለ ግዛቱን በሚገባ ስለሚያውቀውና ስለኖረበትም ለበረዶው የሰጠው ገለጻ ተጋነነ የሚሰኝ አይደለም::

በበረዶው ምክንያት የተቋረጠው የአውሮፕላኖች በረራ ትልቅ ችግር ቢፈጥርም ሐኪሞቹ አንዴ ቆርጠዋልና በነፍስ ለምትጠብቃቸው ጨቅላ ሕጻን የሚቻለውን ሁሉ ዘዴ በመሞከርና እጅግ ኃላፊነትን የሚጠይቅ እርምጃ በመውሰድ የተሰረዘው በረራ እንዲቀጥል ተወስኖ የአማንዶ ልብ ለቲያና እንዲደርስ ተደርጓል:: የሟቹ ልብ ወደ ችካጎ ሆስፒታል እንደደረሰም ሐኪሞች በርብርብ የልብ ነቀላውንና ተከላውን በተሳካ ሁኔታ አከናውነው ለመሞት ስድስት ሰዓት ብቻ የቀራት ቲያና በሕይወት ተርፋ የቤተሰቡ ሀዘን ሊገፈፍ ችሏል::

ይህ ክስተት ከተፈጸመ ሦስት ዓመት በኋላ የሟች ልጇን የአማንዶን ልብ የለገሰቸው እናት፣ ልቡ ለልጃቸው የተበረከተላቸው የቻርለስ ቲልማን ቤተሰቦችና እድለኛዋ ቲያና፣ የኦፕራ ዊንፍሬ በርካታ ታዳሚዎችና በርካታ የሚዲያ ባለሙያዎች በታደሙበት ሥነ ሥርዓት ላይ ሁለቱ ቤተሰቦች ተገናኝተው ምን እንደተሰማቸው ስሜታቸውን እንዲገልጹ የፕሮግራሙ መሪ ኦፕራ ትጠይቀቸው ጀመር::

የእምባ ሣግ እየተናነቃቸው መጀመሪያ ተሽቀዳድመው ሃሳባቸውን የገለጹት የቲያና እናትና አባት ነበሩ:: “ልጃችን በሕይወት እንድትኖር የሟች ልጅሽን ልብ በቸርነትና በርህራሄ ስለ ለገስሽን በጣም እናመሰግናለን::...” የአማንዶ እናት የምሥጋና ንግግራቸውን ሳታስጨርስ ጣልቃ በመግባት “ምሥጋናውን በአክብሮት ተቀብያለሁ:: ‹የሟች ልጅሽን› በማለት በገለጻችሁት ሃሳብ ግን አልስማማም::” ወደ ሕጻኗ ቲያና እየጠቆመች “ልጄ እኮ አልሞተም:: በቲያና ልብ ውስጥ ሲተነፍስ እያደመጥኩት ነው::

”እናንተስ ትርታው አይደመጣችሁም? በፍጹም ልጄ እንደሞተ አላስብም:: ምክንያቱም በቲያና ውስጥ ሕያው ሆኖ እንደሚኖር እርግጠኛ ነኝ::” ይህንን ፕሮግራም ስቱዲዮ ውስጥ በአካል ተገኝተው የሚመለከቱት ብቻ ሳይሆኑ በየቤታቸው ተቀምጠው ፕሮግራሙን የሚከታተሉ ታዳሚዎች ስሜታቸውን የገለጹት እየተንሰቀሰቁ በማልቀስ ነበር::

ሁለቱ ቤተሰቦች ተነስተው ሲተቃቀፉማ የነበረውን ስሜት በቃላት ለመግለጽ በእጅጉ ይከብድ ነበር:: “ልጄ አልሞተም! በቲያና ልብ ውስጥ ሲተነፍስና ትር ትር ሲል ይሰማኛል! እናንተስ አይሰማችሁም?” ይህ ዓረፍተ ነገር በጊዜው በብዙዎች ዘንድ ተደጋግሞ የሚጠቀስ ኃይለ ቃል ነበር::

### ልብ ያለው ልብ ያድርግ፤

የኢትዮጵያ ልብ በጽኑ እየታመመ ይመስላል:: ህመሙ የጸናባት ይህቺ ምስኪን ሀገር ከእለት ወደ እለት መከራ አታጣም:: በሽታው አልጋ ላይ ባይጥላትም እንደ ልብ እንዳትሆንና ሕዝቦቿ በሰላም ተረጋግተው እንዳይኖሩ የተወሳሰበው ህመሟ ፋታ ሊሰጣት ከቶውንም አልቻለም::

ፖለቲካውም ህመሟን አክሞ ልቧን ሊፈውስላት አቅም አጥቷል:: ኢኮኖሚውም ሆነ ማሕበራዊ መስተጋብሩ ልባቸው ፈሶ ልባችንን ካፈሰሱት ውለው አድረዋል:: ነገራችን ሁሉ “ልብ ሲያውቅ ገንፎ ያንቅ” እንዲሉ፤ ሀገር ስትታመም አብረን እህህ የምንለው መፍትሔው ጠፍቶን ሳይሆን የልብ ሀሞታችን ስለፈሰሰ ብቻ ነው::

ለልብ ህመማችን የነበረን አንድ ተስፋ ከምድርም አሻግሮ በዘለዓለሙ የጽድቅ መንገድ ይመራናል እያልን የምንተማመንበት አንድ ቀሪ ሞገሳችን የየግላችን ሃይማኖት ነበር:: የምንተማመንበት እምነታችንም ራሱ ታማሚ ሆኖ በማቃሰት ላይ እንደሆነ “ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ” እንዲሉ ካልሆነ በስተቀር ያንዣበበውን አደጋ እየሰማንም እያየንም ነው::

ተስፋ በማድረግ እንጽናና የነበረው የሕያው ፈጣሪ ቃል በሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ምክር ነበር:: “አዲስ ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ እኖራለሁ:: የድንጋይ ልባችሁን ከእናንተ አስወግዳለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ” (ሕዝቅኤል ምዕ. 36፡26):: የሚለው ዋስትና ትልቁ ማረፊያችን እንደሆነ ስናምን ብንኖርም ዛሬ ዛሬ “ሁሉም ከንቱ የከንቱ ከንቱ” ያለው ጠቢቡ ሰሎሞን ለካስ ቢቸግርው ነው እንድንል ተገደናል::

እለት በእለት እያየን ያለነው “ሰላም ያለው ልብ ለሰውነት ሕይወት” መስጠቱን ሳይሆን “ቅንአትና እብሪት አጥንትን እያነቀዘ” (ምሳሌ 14፡30) ጤና ማጣታችንን ነው:: በሁሉም የማሕበራዊ መስተጋብራችን ውስጥ ገኖ የሚስተዋለውና የሚተገበረው ለሌላው በጎነት ከመኖር ይልቅ መግደልና መጋደል፣ ጠብ መጫርና ማጋጋል፣ ሻምላ መዝዞ በመፋለም ጥሎ ለመውደቅ መጨከንን ነው::

የኢትዮጵያ ልብ ክፉኛ ታሟል:: በዚሁ ጋዜጣ የጥር 27 ቀን 2015 እትም በጥልቀት ለመፈተሽ እንደተሞከረው የልጆቻችን አእምሮ የሚገራበትና የሚሰለጥንበት የትምህርቱ ዘርፍ የልብ ህመሙ ጠንክሮበት ጭራሹኑ ከመቃብር አፋፍ መድረሱን ያረጋገጥነው በልጆቻችን የአሥራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ውጤት መሆኑን በዝርዝር ዳሰሳ ቅኝት ማድረጋችን አይዘነጋም:: የኑሯችንን ጉዳይ ከጨማመርንበትማ ልባችን አንደኛውን ፈስሶ እንደወጣን እንዳንቀር በእጅጉ ያሰጋናል::

ልብ ሊፈስ ይችላል እንዴ? ተብለን የምንሞገት ከሆነ ለዋቢነት የምንጠራው “ልቤ ፈሷል” እያልን በአዘቦት ቀናት የምንግባባበትን እድሜ ጠገብ ብሂላችንን ነው:: ይህንን ጠነን ያለ መከራከሪያ ውድቅ ለማድረግ የኢትዮጵያ ልብ አልታመመም፤ አልፈሰሰም እያሉ የሚከራከሩ ካሉ የአደባባዩ በር ወለል ተደርጎ ይከፈትላቸውና ባመኑበት እውነታ ሊሞግቱን ከመረጡ እንኪያ ሰላንትያውን ልንገጥም ፈቃደኞች ነን::

የእረፍት አልባዋን ሀገሬን ታሪክና እውነታ ለማነጻጸር የምሞክረው የግብጹን ታላቅ ፈርኦን የሴሶስትሪስን ሕልም በማስታወስ ይሆናል:: ቅዱስ መጽሐፍ ታሪኩን የሚያስነብበን በሚከተለው ውብ ትረካ ነው:: “እነሆ በሕልሜ በዐባይ ወንዝ ዳር ቆሜ ነበር:: ሥጋቸው የወፈረና መልካቸው ያማረ ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው በወንዙ ዳር የበቀለውን ሣር ሲግጡ አየሁ:: ከእነርሱም በኋላ፣ አቅመ ደካማ፣ መልካቸው እጅግ የከፋና አጥንታቸውም ያገጠጠ ሌሎች ሰባት ላሞች ወጡ::

“እነዚያን የመሰሉ የሚያስከፉ መልክ ያላቸው ላሞች በግብጽ ምድር ከቶ አይቼ አላውቅም:: አጥንታቸው የወጣና አስከፊ መልክ ያላቸው ላሞች መጀመሪያ የወጡትን ሰባት ያማሩ ላሞች ዋጧው:: ከዋጧቸውም በኋላ ያው የበፊቱ መልካቸው ስላልተለወጠ እንደዋጧቸው ማንም ሊያውቅ አይችልም ነበር::”

ይህ የቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ ለኢትዮጵያ የየዘመናቱ ጉዞ ጥሩ ማነጻጸሪያ መሆን ይችላል:: የሚያማምሩና የሚያስጎመጁ ሀገራዊ ስኬቶች ታዩ ብለን መስክረን ሳንጨርስ እንዴትና ስለምን እንዲያ ሊሆን ቻለ? የምንለው አዲስ አውዳሚ ክስተት ተፈጥሮ ተስፋችንን ውጦ ሀገሪቱን በእርቃኗ ሲያስቀራት ከታሪካችን ደጋግመን ተምረናል::

የደርግ መንግሥት የገጠርን መሬት ለአራሹ ባለ ሀገር እንዲመለስ በአዋጅ ሲያጸና፣ የከተማ ትርፍ ቤትና ቦታ ለደሃው ዜጋ ሲደለድል፣ የሱማሊያ ወረራ ተቀልብሶ ጉሮ ወሸባዬ እየተባለ ሲዘፈን ወዘተ... አብዛኛው ዜጋ “እንብል ሃሌሉያ ታላቅ የመሥራች” እያለ እንደዘመረ ጉደኛው እድሜያችን ለጉድ ጎልቶ ሁሉንም አሳይቶናል:: “የሃሌሉያውን” ፍንደቃ አጨብጭበን ሳንጨርስ ወታደራዊው መንግሥት የጭቃ ጅራፉን አንስቶ እንደምን “አንድ ትውልድ” እምሽክ አድርጎ እንደጎረሰ የሚረሳ አይደለም::

የወታደራዊውን በትረ ሥልጣን ነጥቆ ሀገር ለመምራት የበቃው የወያኔ/ኢህአዴግ አስተዳደር ይህን ያህል ኪሎ ሜትሮች መንገድ ገንብቼ፣ ኮንዶሚኒዬም አስፋፍቼ፣ ዩኒቨርሲቲዎችን አበራክቼ፣ በዲሞክራሲ ሕዝቡን አረስርሼ ወዘተ... እያለ ሲፎክር “በእምበር ተገዳላይ” ዝላይ ብዙዎች አብረነው በከበሮው ድምቀት እስክስታ ወርደናል::

ውሎ አድሮ ግን ሕዝቡን በጊንጥ እየገረፈ ዜጎችን ብቻ ሳይሆን ሀገሪቱን ራሷን ውጦ እርቃኗን ሲያስቀራት ስናስተውልም ጨኸታችንን ወደ ጸባኦት አዥጎድጉደን ፈጣሪ ስለተለመነን ኢትዮጵያ አንገቷን ቀና ማድረግ ጀመረች ብለን ተስፋ ጥለን ነበር:: ደስታችን ውሎ ሳያድር ምን “ጉድ” እንደተፈጠረ የምናውቀው ስለሆነ አልደግመውም:: በእነዚህ ሥርዓቶች ኢትዮጵያ የልቧ ህምም ብሶባት ከሞት አፋፍ እንደተመለሰች የትናንትናና የዛሬ ታሪካችን ስለሆነ ለትዝታ ወግ እንኳን አልደረሰም::

ከሲታዎቹ የሕልመኛው ላሞች የወፈሩትን ላሞች እንደዋጡና ውጠውም አንዳች ለውጥ እንዳላመጡ ሁሉ ይኼኛው የእኛ ዘመንም አፉን ከፍቶ የዋጣቸው ብዙ መልካም ጉዳዮቻችን ተዘርዝረው የሚያልቁ አይደሉም:: ስለዚህም ኢትዮጵያ ልቧ ቆስሏል፤ ክፉኛም ታሟል:: የፈውስ ያለህ እያለች የምትማጸንባቸው ጉዳዮቿም የትዬለሌዎች ናቸው::


ሊሞት ለሚያጣጥረው የተስፋችን ልብ መፈወሻ እንዲሆን ባለ መልካም ልቦች ካልታደጉን በስተቀር ሀገሬ ጤና ስለማግኘቷ እጠራጠራለሁ:: ሀገሬ እየቃተተች ያለችው መልካም “ፖለቲከኞች” እንዲታደጓት ሳይሆን ባለ ልበ ብርሃን “ባለጸጎች” እንዲታደጓት ነው:: “ልብ” ስንል በአማካይ የእጃችንን ጭብጥ የምታህለውንና 320 ግራም ያህል የምትመዝነውን፣ በቀን ውስጥ ወደ 7570 ሊትር ደም በሰውነታችን ውስጥ የምትረጨውንና በአንድ ጎልማሳ ሰው አማካይ ዕድሜ በዓመት 1.5 ሚሊዮን ጋሎን ደም በደም ሥሮቻችን እንዲዘዋወር ምክንያት የሆነችውን ሚጢጢዬ ሥጋዊ አካላችንን ማለታችን አይደለም::

“የኢትዮጵያ ልብ” በማለት በዘይቤያዊ አገላለጽ የወከልነው ከላይ ካናቱ መሪዎቻችንን፣ ከመሃል ያገለግሉናል ብለን ካርዳችንን ያባከንባቸውን ሹማምንቶቻችንን፣ የሃይማኖት መሪዎቻችንን፣ ምሁራንንና የሀብት ባለጸጎችን፤ ወደ ታች ላቡን ጠብ አድርጎ የሚያገለግለው ሠርቶ አደር፣ ገበሬ፣ የየኪዮስካችን ነፍስ አድን ነጋዴዎች ወዘተ... ማለታችን ነው:: እውነት እውነቱን እንነጋገር ካልን ማን ያልታመመ አለ? ማንስ ህመሙ ጸንቶበት የማያቃስት አለ? ካለ መልካም! ግን ያለ አይመስለንም::

ስለዚህም ኢትዮጵያ ታማለች፤ ያውም ልቧን:: መፍትሔዋ የሚመጣው በጤነኛ ልብ የሚመሩን፣ የሚያገለግሉን፣ በፈረሰው በኩል ቅጥሯን ለመድፈን የሚታትሩ ዜጎች ሲበረክቱ ነው:: የወንጀለኛና የፍትሐ ብሔር ሕግ እየጠቀሱ፣ በሕገ መንግሥት ሰነድ እያስፈራሩ አንገት የሚያስደፉንን ሳይሆን ለእውነት ኖረው ለእውነት የሚሞቱ ጥቂት ባለ መድኃኒቶች ተገኝተው ለብዙኃን የልብ ህመም ፈውስ መሆን ሲችሉ ብቻ ነው:: ሰላም ለሕዝባችን፣ በጎ ፈቃድ ለዜጎቻችን::

# የቅመማ ቅመም ምርት - ቀጣዩ የወጪ ንግዱ ተስፋ

ፍሬሕይወት አወቀ



ግብርና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት መሆኑ ይታወቃል:: የዚህ ምክንያቶቹም 83 በመቶ የሚሆነው ኢትዮጵያዊ የዕለት ጉርሱንና የዓመት ልብሱን የሚያገኘው እንዲሁም ቤተሰቡን የሚያኖረው ከዚሁ ከግብርና ዘርፍ በሚያገኘው ገቢ በመሆኑ ነው:: ሀገሪቱ ለውጭ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ከምታገኝባቸው ምርቶች ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑት የግብርና ምርቶች ናቸው::

ከእነዚህ የግብርና ምርቶች መካከል በቀዳሚነት እየተጠቀሱ ከሚገኙት የቡና እና የአበባ ምርቶች በተጨማሪ የቅመማ ቅመም ምርትም ለውጭ ገበያ በመቅረብ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ይታወቃሉ:: ከግብርና ምርቶች መካከል በቅመማ ቅመም ዘርፍ ተጠቃሽ ከሆኑትና ወደ ውጭ ገበያ ከሚቀርቡት ውስጥ ዝንጅብል፣ በርበሬ፣ ኮረሪማ፣ ጥምዝ እርድ፣ ቁንዶ በርበሬ፣ ሄል፣ አብሽና ድንብላል ይገኙበታል::

ከቡናና ሻይ ባለስልጣን የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ በዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃ ተቋም ተለይተው ከቀረቡት 109 ከሚደርሱ የቅመማ ቅመም ምርቶች፤ መዓዛማ ተክሎችና የቅመማ ቅመም ቤተሰቦች ከ50 በላይ የሚሆኑት በኢትዮጵያ የሚመረቱ ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥም 23 የሚደርሱት ቅመማ ቅመሞች በጥሬያቸውና እሴት ተጨምሮባቸው ለውጭ ገበያ እየቀረቡ ለአገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ እያስገኙ መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ::

ለአገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ እያስገኘ ያለው ይህ የቅመማ ቅመም ምርት በአገሪቱ እንዴት እየለማ ነው፤ የግብይት ሂደቱስ ምን ይመስላል፤ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው ሚና እንደምን ያለ ነው? በእዚህ ላይ የዘርፉ ባለሙያዎች ምን ይላሉ?

በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የቅመማ ቅመም ልማት ዴክስ ኃላፊ አቶ ሞገስ አሸናፊ የአገሪቱ እምቅ ሃብት የሆነው የቅመማ ቅመም ምርት በተለመደው የአስተራረስ ዘዴ እየለማ ውስን በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ይውል እንደነበር ያስታውሳሉ::

እሳቸው እንዳሉት፤ ይህም ሲባል ታዲያ እናቶች በትንሽ ቦታና አጥር ጥግ ለመድሃኒት በሚል የሚያለሙት አሰራር ነው የተለመደው:: አሁን ላይ አርሶ አደሩን በማስተማርና ግንዛቤ በማስጨበጥ የቅመማ ቅመም ምርት በስፋት እንዲያለማ እየተደረገ ነው:: ምርቱን ወደ ውጭ ገበያ በመላክም አገሪቷ ከዘርፉ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት እንድትችል እየተሰራ ይገኛል:: በዚህም መሰረት አርሶ አደሩ ግንዛቤውን እያገኘ ሰፊ በሆነ የእርሻ መሬት ላይ የተለያዩ ቅመማ ቅመሞችና መአዛማ ተክሎች በማልማት ከአገር ውስጥ ፍጆታ በተጨማሪ ወደ ውጭ ገበያ በማቅረብ ላይ ነው::

በአገሪቱ በስፋት ከሚመረቱት የቅመማ ቅመም ምርቶች መካከል በርበሬ፣ ድንብላል፣ አብሽ፣ ነጭ አዝሙድ፣ ጥቁር አዝሙድ፣ ኮረሪማ፣ እርድ፣ ዝንጅብልና ሌሎችም ተጠቃሽ እንደሆኑ ያነሱት አቶ ሞገስ፤ እነዚህ ቅመማ ቅመሞች ለውጭ ገበያ እንደሚቀርቡ ያመለከታሉ፤ የእነዚህን ቅመማ ቅመሞች ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የገበያ ተደራሽነታቸው እንዲሰፋ የመደገፍ ሥራ እየተሠራ መሆኑንም ይናገራሉ::

እንደ አብሽ፣ ድንብላል፣ ነጭ አዝሙድና ጥቁር አዝሙድ የመሳሰሉት በአገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች ማለትም ጎንደር፣ ሸዋና ባሌ አካባቢ በስፋት እንደሚለሙ ተናግረው፣ እንደ ዝንጅብልና እርድ የመሳሰሉት ደቡብ ላይ በስፋት የሚለሙ መሆናቸውን ይገልጻሉ:: ዝንጅብል በበሽታ ምክንያት በ2004 ዓ.ም አካባቢ ሙሉ ለሙሉ ጠፍቶ አደጋ ውስጥ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ሞገስ፤ ካለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ወዲህ በሽታውን ለመቆጣጠር በተደረገው ጥረት አርሶ አደሩም እያንሰራራ ይገኛል ይላሉ:: ለውጭ ገበያ ያለው ተደራሽነት እንደ ቀደመው ጊዜ የሚያበረታታ እንዳልሆነም ነው ያስታወቁት:: እንደ እርድ፣ በርበሬና የመሳሰሉት ቅመማ ቅመሞች ግን ጥሩ የገበያ ዕድል እንዳላቸው ተናግረዋል::

የቅመማ ቅመም ግብይትን አስመልክቶ ምላሽ የሰጡን በቡናና ሻይ ባለስልጣን የቅመማ ቅመም ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ካሳሁን ገለታ እንዳሉት፤ በአሁኑ ወቅት ወደ ውጭ ገበያ የሚላኩት የቅመማ ቅመም ምርቶች በመጠንና በጥራት እየጨመሩ ሲሆን፤ አገሪቷም ከዘርፉ የምታገኘው ገቢ እያደገ መጥቷል::

በዋናነት ወደ ውጭ ገበያ ከሚላኩት የቅመማ ቅመም ምርቶች በተጨማሪ በጉምሩክ መረጃ ውስጥ የሚካተቱ ሌሎች የቅመማ ቅመም ምርቶች መኖራቸውን ነው አቶ ካሳሁን የጠቆሙት:: በዚህም መሰረት በተያዘው በጀት ዓመት እንደ አገር በጥቅሉ 14 ሺ 896 ቶን መታቀዱን ጠቅሰው፣ ከዚሁ ምርት ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀው ገቢም 20 ሚሊዮን ዶላር እንደሆነ ተናግረዋል:: እስካሁን ባለው የገበያ ሂደትም ባለፉት ስድስት ወራት አራት ሺ 727 ሜትሪክ ቶን ቅመማ ቅመም መላክ የነበረበት መሆኑን አስታውሰው ሶስት ሺ 374 ሜትሪክ ቶን በመላክ የዕቅዱን 71 በመቶ ማሳካት ተችሏል ሲሉ ያብራራሉ:: ይህም ከገቢ አንጻር ሰባት ነጥብ 03 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማግኘት እንደተቻለና የእቅዱን 78 በመቶ ማሳካት መቻሉን ነው የተናገሩት::

አሁን ላይ የቅመማ ቅመም ምርት ግብይት አንዱ የመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ እየተሠራበት ይገኛል ያሉት አቶ ካሳሁን፣ ባለፉት ዘመናት የቅመማ ቅመም ዘርፉ ልክ የህግ ማዕቀፍ እንዳልነበረው ይገልጻሉ:: በዚሁ ምክንያትም በገበያ ውስጥ አነስተኛ ድርሻ እንደነበረው ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ የቅመማ ቅመም ግብይት የሚመራበት የግብይት መመሪያ ወይም የህግ ማዕቀፉ እየተዘጋጀ መሆኑንም አስታውቀዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ እስካሁን በነበረው የገበያ ሂደት በተለይም ለዘርፉ የተዘጋጀና ግብይቱ የሚመራበት የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ችግሮች ነበሩ:: ይሁንና አሁን ላይ መንግሥት የትኩረት አቅጣጫውን ሙሉ ለሙሉ በቅመማ ቅመም ላይ በማድረግ አምራች ክልሎችን ጨምሮ የግብይት መመሪያውን ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሠራ ነው:: የግብይት መመሪያው ሥራ ላይ ሲውልም በውስጡ የሚይዛቸው በርካታ ፓኬጆች ስለመኖራቸው የጠቀሱት አቶ ካሳሁን፤ ከፓኬጆቹ መካከልም የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላትን ጨምሮ የግብይት ተዋናዮች እነማን ናቸው፤ ከአምራቹ በቀጥታ የሚገዛው ማን ነው፤ ከእነሱ የሚረከቡትስ እነማን ናቸው የሚሉትና ሌሎችም ተካተውበታል ሲሉ ያብራራሉ::

በአገሪቱ በቅመማ ቅመም ግብይት ተሰማርተው ምርቱን ወደ ውጭ ገበያ የሚልኩ ከ100 የሚበልጡ ላኪዎች ስለመኖራቸው የጠቀሱት አቶ ካሳሁን፤ እነዚህንና ሌሎችንም የዘርፉ ተዋናዮች የማገናኘትና ህጋዊ የማድረግ ተግባር እንደሚከናወን አመልክተዋል:: የእስከ አሁኑ የገበያ ሂደት ችግሮች እንዳሉት በመጥቀስም አሁን ላይ ችግሮቹን ለመቅረፍ እየተሰራ ነው ብለዋል::

አቶ ካሳሁን እንዳስታወቁት፤ ወደ ውጭ ገበያ በስፋት ከሚላኩት የቅመማ ቅመም ምርቶች መካከልም በርበሬ፣ ዝንጅብል፣ እርድ፣ ኮረሪማ፣ ነጭ አዝሙድ፣ ጥቁር አዝሙድ በዋናነት ይጠቀሳሉ::

የቅመማ ቅመም ምርት የገበያ ሂደትን በተመለከተ አምራቾቹ ምርቱን ለመሰረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት ያቀርባሉ:: መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት ደግሞ ምርቱን አዘጋጅተው ወደ ውጭ ለሚልኩ ላኪዎች በማቅረብ ግብይቱ ይከናወናል::

እነዚህ ቅመማ ቅመሞች ከአገር ውስጥ ገበያ ባለፈ ወደ ውጭ ገበያ ሲላኩ በጥሬያቸውና እሴት ተጨምሮባቸው መሆኑን የገለጹት አቶ ካሳሁን፤ እሴት የተጨመረባቸው ምርቶች ወደ አሜሪካ፣ ህንድ፣ ካናዳ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ፣ ኢንዶኔዥያ፣ እስራኤልና እንግሊዝ እንደሚላኩ ገልጸዋል:: የምርቶቹ መጠን ይብዛ አልያም ይነስ እንጂ 28 ለሚደርሱ የዓለም አገራት የኢትዮጵያ ቅመማ ቅመሞች ተደራሽ መሆናቸውንም ያመለከታሉ::

በስፋት ወደ ውጭ ገበያ እየቀረቡ ካሉትና ከላይ ከተዘረዘሩት ቅመማ ቅመሞች በተጨማሪ በቅርቡ በተለምዶ የስጋ መጥበሻ ቅጠል ወይም አዝሞሪኖ በስፋት እየለማና ወደ ገበያ እየገባ እንደሆነ ያነሱት አቶ ካሳሁን፤ ምርቱ በስፋት እየተመረተ ያለውም በስልጤ ዞን አካባቢ በኩታ ገጠም እርሻ መሆኑን ይጠቁማሉ፤ ይህ በክላስተር እየተመረተ ያለ ሰፊ የአዝሞሪኖ ምርት ገበያ ማግኘት እንዲችልና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር እየተሰራ እንደሆነም አስረድተዋል::

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በአገር ውስጥ የሚሸጠው ምርት እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ውጭ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ማምጣት እንዲችል ጥረቶች እየተደረጉ ናቸው:: ይሁንና ቻይና የአዝሞሪኖ ምርትን በስፋት እያመረተች የዓለም ገበያ ፍላጎትን ለማሟላት በስፋት እየሄደችበት ነው:: ከቻይና በተጨማሪም ሞሮኮና ሌሎች አፍሪካ አገራትም ምርቱን በስፋት የሚያመርቱ በመሆናቸው ኢትዮጵያም በአዝሞሪኖ ምርት የውጭ ገበያ ውስጥ መግባት እንድትችል ብዙ መሠራት ያለባቸው ሥራዎች አሉ::

ተፎካካሪና ተወዳዳሪ ከሆኑ አገራት ጋር በመሆኑ ገበያውን ሰብሮ ለመግባትና በተሻለ ዋጋ ለመሸጥ የሚቀሩ ነገሮች ቢኖሩም፣ እንቅስቃሴዎች ስለመኖራቸውም ነው አቶ ካሳሁን የሚናገሩት:: ከዚህም ባለፈ በተወሰነ መጠንም ቢሆን ምርቱን ወደ ውጭ ገበያ የላኩ እንዳሉም አንስተዋል:: ይሁንና ባለፉት ስድስት ወራት ብዙ ተልኳል ማለት ባያስደፍርም በስድስት ወራት ውስጥ ወደ ውጭ ከተላኩ የቅመማ ቅመም ምርቶች መካከል ሶስት ኮንቴነር አዝሞሪኖ ስለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ::

በጅምር ላይ ያለውን የአዝሞሪኖ ልማት በማስፋፋት ተፎካካሪ በመሆን ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ብዙ ሥራ መሠራት እንዳለበት ያስገነዘቡት አቶ ካሳሁን፤ ምርቱን በጥራት በማምረት በውጭ ገበያው ተወዳዳሪ መሆን እንደሚቻልም ነው ያስረዱት::

የቅመማ ቅመም ምርት የሚመራበት የህግ ማዕቀፍ እየተዘጋጀ መሆኑ ለዘርፉ ዕድገት ወሳኝ እንደሆነ በማንሳት፤ የግብርና ሚኒስቴር የግብይት መመሪያውን በቅርቡ የሚያጸድቅ መሆኑንም አቶ ካሳሁን ጠቁመዋል:: መመሪያው እንደጸደቀም እስከ ታች ድረስ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንደሚሰሩም ተናግረዋል:: ወደ ውጭ የሚላኩ የቅመማ ቅመም ምርቶች የጥራት ደረጃቸው የተዘጋጀ በመሆኑም ከህግ ማዕቀፉና ከመመሪያው ጋር አዛምዶ እንደሚሰራ አስታውቀው፣ ይህንኑ አጠናክሮ በመቀጠልም የቅመማ ቅመም ምርቶችን ከሌሎች ተፎካካሪ አገራት ጋር ተወዳዳሪ መሆን እንዲችል፤ በጥራትና በስፋት አምርቶ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ለመሆን ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው ብለዋል::

እንደ አቶ ካሳሁን ገለጻ፤ በአገሪቱ በርካታ የቅመማ ቅመም አይነቶች እየተመረቱ ለውጭ ገበያ ሲቀርቡ ቆይተዋል:: ከውጭ አገርም በተመሳሳይ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የቅመማ ቅመም ምርቶች አሉ:: በመሆኑም በአገር ውስጥ የሚመረቱ የቅመማ ቅመም ምርቶችን እሴት በመጨመር ከውጭ የሚመጡትን የቅመማ ቅመም ምርቶች በአገር ውስጥ ለመተካት ይሰራል:: ለአብነትም የሮዝመሪ ዘይት ለማምረት ባለሃብቶች ማሽን በማስገባት ሂደት ላይ ይገኛሉ:: ይህም ከአገር ውስጥ ፍላጎት ባለፈ ወደ ውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚደረግ ሂደት በመሆኑ ተጠናክሮ ይቀጥላል::

አገሪቷ እስካሁን በነበረው ሂደት ከቅመማ ቅመም ምርት ማግኘት የሚገባትን ገቢ ማግኘት እንዳልቻለች የጠቀሱት አቶ ካሳሁን፤ ለአብነትም ባለፈው በጀት ዓመት ከምርቱ የተገኘው ገቢ 16 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደነበር አስታውሰዋል:: ይሁንና በቀጣይ በደንብ መሰራት ከተቻለ ከዚህ በበለጠ ገቢ ማግኘት ይቻላልም ብለዋል::

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የማህበራዊ ገጾች ቋንቋ

**ዋለልኝ አየለ**

ማህበራዊ የመገናኛ ዘዴዎች በአጭር ዓመታት ውስጥ በዓለም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ መፍጠር ችለዋል። እንደ ኢትዮጵያም ካየን በአሁኑ ጊዜ የማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች ከፍተኛ ተከታይ አላቸው። እንዲያውም ከመደበኛዎቹ መገናኛ ብዙኃን ቀድመው እየታዩም ነው። ከእነዚህ ማህበራዊ የመገናኛ ዘዴዎች ውስጥ በስፋት የወጣቱን ቀልብ የተቆጣጠረው ፌስቡክ ሆኖ የቆየ ቢሆንም አሁን ግን ‹‹ቲክቶክ›› የሚባለው ተጨምሯል።

ፌስቡክ በጣም ብዙ ተብሎለታል። በመድረክም ይሁን በዋናዎቹ የመገናኛ ብዙኃን ስለፌስቡክ ጠንካራም ሆነ ደካማ ጎን ብዙ ተብሏል። ክርክሮችም ነበሩበት። ክርክሮቹ ግን የተለያዩ አይነት ናቸው። መጀመሪያ ፋሽን በነበረበት ጊዜ የነበረው ክርክር ‹‹ጊዜን ያባክናል እንጂ ምንም አይጠቅምም›› የሚሉ እና ‹‹በራሱ ማንበብ ስለሆነ ጊዜን ማባከን አይደለም›› የሚሉ ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ‹‹ውሸትና አሉባልታ የሚነዛበት ነው፣ ብሔርን ከብሔር እያጋጨ ነው›› የሚሉ እና ‹‹መደበኛዎቹ የመገናኛ ብዙኃን በጣም ይዘገያሉ፣ እውነቱን አያሳውቁም፤ ስለዚህ ፌስቡክ አማራጭ ነው›› የሚሉ ናቸው።

ለሁሉም ክርክሮች እንደ አስታራቂ የሚወሰደው ሀሳብ ‹‹እንደ አጠቃቀሙ ነው›› የሚለው ነው። እርግጥ ነው እንዳጠቃቀሙ ነው፤ ግን የሚያጠፋው ከበለጠ ደግሞ ችግር ነው። እንደ አጠቃቀሙ ነው የሚባለው ለግለሰብ ነው። ለምሳሌ እኔ ጥሩ ጥሩ ነገር ብቻ እየፈለኩ የማነብበት ከሆነ፣ ጊዜዬን በአግባቡ የምጠቀምበት ከሆነ ጠቀሜታው ለእኔ ብቻ ነው። እንደ አገር እያስከተለ ያለውን ችግር ማስቀረት የሚቻለው ግን ሁሉም ባይሆን እንኳን ቢያንስ አብዛኛው በአግባቡ ቢጠቀም ነበር።

ለማንኛውም ፌስቡክም ሆነ ሌሎች የማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች እያስከተሉ ካለው አሉታዊ ችግር ውስጥ እኔ መታዘብ የፈለኩት የቋንቋ አጠቃቀምን ነው። ይሄ ነገር ብዙም ትኩረት የተሰጠው አይመስለኝም። ዳሩ ግን ቋንቋን በጣም እያበላሹ ነው። ውሸት እየተደጋገመ ሲሄድ እውነት መምሰሉ ግልጽ ነው። በተመሳሳይ ስህተት በጣም በተደጋገመ ቁጥር ልክ ሊመስል ይችላል።

ነገሩ ቀላል አለመሆኑን ለማረጋገጥ ይህን ልብ እንበል! ፌስቡክ ላይ ያለውን የተሳሳተ የቋንቋ አጠቃቀም በጋዜጦች፣ መጽሔት፣ ሬዲዮና ቴሌቭዥን ላይ ያሉ ጋዜጠኞች መጠቀም ጀምረዋል። በዚህ አሥራ አምስት ዓመት እንኳን ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ፌስቡክ ይህን ያህል ጥፋት ማድረስ ከቻለ በአርባና ሃምሳ ዓመታት ውስጥ አንድን ቋንቋ ሙሉ በሙሉ ላለማውደሙ እርግጠኞች አይደለንም።

ስህተቱ እኮ እዚያው ፌስቡክ ላይ ብቻ ቢቀር ባልከፋ ነበር። ዛሬ ላይ ጋዜጠኛውም፣ ባለሥልጣኑም፣ ምሁሩም የፌስቡክ ተጠቃሚ ቢሆንም በብዛት የሚጠቀሙት ግን ወጣቶች ናቸው። እነዚህ ወጣቶች ደግሞ ለቋንቋ አጠቃቀም ግዴለሽ እየሆኑ ነው። ጋዜጠኛው ይህን ነገር ማስተካከል ሲገባው ጭራሽ በመገናኛ ብዙኃንም ፌስቡክ ላይ በለመደው እየተጠቀመ ለሚሊዮን ህዝብ ያዳርሳል። አሁን ላይ እኮ ጋዜጦችና መጽሔት ላይ፣ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ ጸያፍ የቃላት አጠቃቀም እያየን ነው።

ለምሳሌ ‹‹መጣህ›› ለማለት ‹‹መጣክ›› ‹‹በላህ›› ለማለት ‹‹በላክ›› እያሉ መጠቀም እየተለመደ መጥቷል። በሌላ በኩል አግባብ ያልሆኑ አብዢ ቅጥያዎችን ማየትም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፌስቡክ ያስፋፋው ስህተት ነው። ‹‹መጣችሁ›› ለማለት ‹‹መጣቹ›› ወይም ደግሞ ‹‹መጣችው›› የሚባልም አለ። ምናለ ስህተቱ እንኳን አንድ አይነት ቢሆን? ‹‹እመጣለሁ›› ለማለት ‹‹እመጣለው›› እያሉ መጻፍ አሁን አሁን እየተለመደ ነው።

እነዚህ ነገሮች እየተለመዱ ሲሄዱ መደበኞቹ አጠቃቀሞች ስህተት ሊመስሉ ይችላሉ ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ታዳጊ በተደጋጋሚ ‹‹እመጣለው›› የሚል ቃል ከሆነ የሚያነብና የሚሰማ ‹‹እመጣለሁ›› የሚል ቃል ቢያገኝ ስህተት ሊመስለው ይችላል ማለት ነው። ‹‹ምን ችግር አለው ይሄኛው ቢለመድና መግባቢያ ቢሆን?›› ይባል ይሆናል። በጣም ችግር አለው። አንደኛ ቀደም ያሉ መጻሕፍትን ማንበብ ላይቻል ነው። ሁለተኛ ደግሞ በጣም ስህተት ስለሆኑ የትርጉም ለውጥ ሁሉ ያመጣሉ። በቋንቋ ምሁራን ከተጠናው የሰዋሰው ህግ ውጭ ይሆናል ማለት ነው።

ለምሳሌ፡- ‹‹በላችሁ›› በሚለው ዓረፍተ ነገር(ቃል) ውስጥ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ‹‹እናንተ›› የሚለው ነው። አሁን ፌስቡክ ባበላሸው የቋንቋ አጠቃቀም ስንሄድ ግን ‹‹በላችሁ›› ለማለት ‹‹በላችው›› ተብሎ ይጻፋል? እዚህ ላይ እንግዲህ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ማነው? ‹‹እናንተ›› ወይስ ‹‹እሷ››? ተመልከቱ እንግዲህ የተፈጠረውን ስህተት! ‹‹እናንተ›› የሚለውና ‹‹እሷ›› የሚለው ተውላጠ ስም ተምታታ ማለት ነው። ሁለቱ ተውላጠ ስሞች ምንም የማይገናኙ ናቸው። ‹‹እናንተ›› ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ሲሆን ‹‹እሷ›› የሚለው ደግሞ ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ነው።

እነዚህ ነገሮች ለጊዜው እንደ ቀላል ይመስሉን ይሆናል፤ ዳሩ ግን ቀስበቀስ ብዙ ጥፋት እያመጡ ነው። ደጋግሜ እንዳልኩት በዋናዎቹ የመገናኛ ብዙኃንም እንደ ትክክል ተወስደው አገልግሎት ላይ እየዋሉ ነው። ይሄ ጋዜጠኛ መጽሐፍ እንኳን ቢጽፍ በዚህ ቋንቋ ነው ማለት ነው የሚጠቀመው።

ሌላው ፌስቡክ በቋንቋ ላይ እያደረሰው ያለው ጥፋት ደግሞ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ነው። ሥርዓተ ነጥብ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ትልቅ ሚና እንዳለው ግልጽ ነው። የትኛውም ቋንቋ የራሱ የሆነ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ሥርዓት አለው። ብዙ ቋንቋዎች በጋራ የሚጠቀሚቸው የሥርዓተ ነጥብ አይነቶች ቢኖሩም አንዳንዶቹ ደግሞ የራሳቸው ሥርዓተ ነጥብ የላቸውም አሉ። በመገናኛ ብዙኃን በስፋት አገልግሎት ላይ እየዋለ ያለው የአማርኛ ቋንቋ የራሱ የፊደል ገበታ ያለውና በአፍሪካ ብቸኛ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገለጽ የቆየ ነው። ይህ ቋንቋችን የራሱ የሆነ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀምም ያለው ነው። አማርኛ ከሌሎች ቋንቋዎች ጋር በጋራ የሚጠቀማቸው የሥርዓተ ነጥብ አይነቶች ቢኖሩም የራሱ ብቻ የሆኑም አሉ።

ፌስቡክ ላይ የሚታየው ግን እንኳንስ የራሱን የሚጠቀሙበትን ቋንቋ የየትኛውንም ቋንቋ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ህግ ያልተከተለ ነው። ሥርዓተ ነጥብን ያለ አግባብ መጠቀም ደግሞ የትርጉም ለውጥ ሁሉ ያመጣል። በአሁኑ ጊዜ ታዳጊዎች ሁሉ የፌስቡክ ተጠቃሚ ሆነዋል። ያለምንም አገልግሎት በቃላት መካከል ውስጥ የተደረተን ሥርዓተ ነጥብ ሲያዩ ትክክለኛ አገልግሎቱ እንደዚያው ሊመስላቸው ይችላል። አንዳንዴ ደግሞ ጭራሽ መሆን የማይገባውን ሥርዓተ ነጥብ ሁሉ ሊጠቀሙ ይችላሉ። በሌላ በኩልም አገልግሎት ላይ ካለመዋላቸው የተነሳ የሌሉ የሚመስሉ ሥርዓተ ነጥቦችን ይረሷቸው ይሆናል።

ለምሳሌ፡- እንደ ድርብ ሰረዝ(፤)፣ ነጠላ ሰረዝ(፣) ሁለት ነጥብ ከሰረዝ(፡-) አቆልቋይ ወይም እዝባር(/)፣ ሁለት ነጥብ(፡) እና የመሳሰሉት ፌስቡክ ላይ አገልግሎት ላይ ሲውሉ አይታይም። የእነዚህን ሥርዓተ ነጥቦች አገልግሎት ቢጠየቅ ብዙ ሰው ግራ ሊጋባ ይችላል።

ለቋንቋና ባህል መበረዝ ብዙ ጊዜ ቴክኖሎጂ ተጠያቂ ሲደረግ ይሰማል። አንድ የቋንቋና ስነ ጽሑፍ ተመራማሪ በዚህ ጉዳይ ላይ በአንድ ወቅት ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸው ነበር። እርሳቸው የነገሩኝ እንዲያውም ቴክኖሎጂ የበለጠ እንዲተዋወቅ የሚያደርግ፣ ለማስተካከል የሚያግዝና የበለጠ አመቺ እንደሆነ ነበር የነገሩኝ። የእርሳቸው ሀሳብ ልክ መሆኑን ደግሞ ጥፋት ቢኖርባቸውም የማህበራዊ ገጾች አሳይተውናል። ብዙ አባባሎችን፣ የፈጠራ ሥራዎችን፣ ቀልዶችን፣... አይተንበታል።

የጽሑፍ የማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች(ለምሳሌ ፌስቡክ) የጽሑፍ ቋንቋ ላይ ከላይ ያየነውን የአጻጻፍ ስህተቶች አስከተሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጡት እንደ ቲክቶክ ያሉ የቪዲዮ መተግበሪያዎች ደግሞ የንግግር የቋንቋ አብዮት ፈጠሩ። ጎልማሶችና አዛውንቶች ሊረዱት የማይችሉት የአነጋገር ቅላጼ ጀመሩ። አዛውንቶች ቲክቶች ስለማያዩ ችግር አልነበረውም፤ የሚያሳዝነው ግን ቲክቶክ ሲከታተሉ የሚውሉ ጋዜጠኞች ሬዲዮ ላይ ወጥተው በዚያው መንገድ እያወሩ ነው። የማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች ላይ ያሉትን ለመታዘብ ባይቻል እንኳን ቢያንስ መደበኛዎቹ መገናኛ ብዙኃን ላይ ያሉት ግን ለሁሉም በሚገባ ቋንቋ ቢያወሩ!

# ዓለም አቀፍ



## ቱርክ ለ7 ቀናት ብሔራዊ ሐዘን አወጀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የቱርኩ ፕሬዝዳንት ረሲፕ ጣይብ ኤርዶሃን የሰባት ቀናት ብሔራዊ የሐዘን ቀን አወጁ።

ወደ 3 ሺህ የሚጠጉ ህንጻዎችን ያፈራረሰው ርዕደ መሬት ከ1999 ወዲህ በቱርክ አውዳሚ መሆኑ የተነገረለት የአገሪቱሐፕሬዝዳንት በትናንትናው እለት በደረሰው የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ሕይወታቸው ያለፈ ዜጎችን ለማሰብ ነው የሐዘን አዋጁን ያወጁት። የቱርክ ባንዲራ እስከ ቀጣዩ ሳምንት ድረስ ዝቅ ብሎ ይውለበለባል ተብሏል።

በሬክተር ስኬል 7 ነጥብ 8 ሆኖ የተመዘገበው ርዕደ መሬት በቱርክ ብቻ ከሁለት ሺህ በላይ ሰዎችን ሕይወት ቀጥፏል፤ የነፍስ አድን ስራው ባለመጠናቀቁም የሟቾቹ ቁጥር እንደሚያሻቅብ ይጠበቃል።

በአደጋው ከ2 ሺህ 800 በላይ ህንጻዎች መፈራረሳቸውን ያነሱት ፕሬዝዳንት ኤርዶሃን፥ ይህም ከፈረንጆቹ 1999 ወዲህ የደረሰ አሰቃቂ አደጋ ያደርገዋል ብለዋል። ኤርዶሃን ከ9 ሺህ በላይ የአደጋ ጊዜ ሰራተኞች ተሰማርተው የነፍስ አድን ስራዎችን መከወናችን ስለመቀጠላቸውም ተናግረዋል።

አንካራ ከ45 ሀገራት እንዲሁም ከሰሜት አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) እና ከአውሮፓ ህብረት የአጋርነት መልዕክት እንደደረሳትም ነው ያነሱት።


ይህ በእንዲህ እንዳለ ቱርክ በሬክተር ስኬል 5 ነጥብ 6 ሆኖ የተመዘገበ ርዕደ መሬት በትናንትው እለት ማስተናገዷ እየተዘገበ የተዘገበ ሲሆን አደጋው ያደረሰው ጉዳት ስለመኖሩ ግን አልተጠቀሰም።

ቱርክ ለመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ከፉኛ ተጋላጭ ከሆኑ ሀገራት መካከል አንዷ ስትሆን በፈረንጆቹ 1999 ኢዝሚት በተሰኘች ከተማ የደረሰ ርዕደ መሬት ከ17 ሺህ በላይ ሰዎችን ሕይወት መንጠቁ የሚታወስ ነው።

በ2011ም በምስራቃዊቷ ቫን ከተማ ከ500 በላይ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈ ርዕደ መሬት መከሰቱን ሮይተርስ ዘግቧል።

## ኬንያዊው በፌስቡክ ኩባንያ ላይ ክስ እንዲመሠርት ተፈቀደለት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- አንድ ኬንያዊ በፌስቡክ የይዘት አርታኢ ሆኖ በሚሠራበት ጊዜ አእምሮን የሚያውኩ ተንቀሳቃሽ ምሥሎችን በብዛት እንዲመለከት በመገደዱ የተነሳ ለደረሰበት ከፍተኛ የአእምሮ ቀውስ የፌስቡክ ባለቤት ሜታ ኩባንያን እንዲከስ የኬንያ ፍርድ ቤት ወሰነ።

ዳንኤል ሙታንጉ የሚባለው ይህ ኬንያዊ አእምሮ አዋኪ ይዘቶችን ፌስቡክ ላይ እንዲቆጣጠር ይከፈለው የነበረው በሰዓት 2 ነጥብ 2 ዶላር ብቻ ነበር። ይሁንና የሥራ መደቡ ሰዎች ሰዎችን በጭካኔ ሲገድሉ፣ ሕጻናት ጾታዊ ጥቃት ሲደርስባቸው፤ አንድ ሰው ሌላውን በእሳት ሲያቃጥል እና ከዚህም የከፉ የፌስቡክ ይዘቶችን ተመልክቶ የማጥፋት ሥራ ሲሰራ ነበር፡፡

ዳንኤል ሙታንጉ እንደሚለው ሥራ እንደተቀጠረ ወዲያውኑ የተመለከተውና ያስወገደው የፌስቡክ ቪዲዮ አንድ ሰው የሌላውን ሰውን አንገት ሲቀላ የሚያሳይ ነበር። ይህ ኬንያዊ ይሠራ የነበረው ፌስቡክ ይዘት እንዲቆጣጠርለት ቀጥሮት ለነበረው ሳማ ለሚባል ኩባንያ ነበር። በዚህ ኩባንያ ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ በርካታ ኢትዮጵያዊያን እንዳሉና በሥራ ባሕሪያቸው የተነሳ ለከፍተኛ የአእምሮ መታወክ እንደተጋለጡ ቢቢሲ ከዚህ ቀደም መዘገቡ ይታወሳል።

ዳንኤልን በተመለከተ ሜታ ለፍርድ ቤት ባቀረበው መቃወሚያ የኬንያ ፍርድ ቤት የፌስቡክ ባለቤት የሆነውን ሜታ ኩባንያን ጉዳይ ለማየት ሕግ አይፈቅድለትም፤ ምክንያቱም ሜታ በኬንያ የሚሠራ ድርጅት ስላልሆነ ብሎ ከተከራከረ በኋላ የሜታን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ሜታም ሆነ ሳማ ኩባንያዎች በዚህ ሥራ ሸሪክ ስለሆኑ ሊከሰሱ ይችላሉ ሲል በይኗል።

ሜታ ለቢቢሲ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ቢታቀብም ጠበቆቹ ይህን የኬንያ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ውድቅ ለማድረግ አቤት እንደሚሉ ይጠበቃል። በፈረንጆቹ 2020 ሜታ በአሜሪካ ተመሳሳይ ክስ ቀርቦበት 52 ሚሊዮን ዶላር ክፍያ በድርድር ካሳ በመክፈል የፍርድ ሂደት እንዲዘጋ ማድረጉ ይታወሳል።


ፌስቡክ በሺህ የሚቆጠሩ የይዘት አርታኢዎች በመላው ዓለም ያሉት ሲሆን ተግባራቸውም ሕግና ደንብን የሚጻረሩ ይዘቶች ሲለጠፉ በቶሎ ማስወገድ ነው።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## አምሃ ተወዳጅ- የመድረኩ ቀንዲል

ማህሌት አብዱል



ኢትዮጵያ በሙያቸው ሀገራቸውንና ወገኖቻቸውን ቀና ያደረጉ በርካታ የኪነ-ጥበብ ሰዎች አሏት:: ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የልፋታቸውን ያህል ቦታና ክብር ሲሰጣቸው አይታይም:: በዚህም ጥቂት የማይባሉት በእድሜያቸው መባቻ አስታዋሽ አጥተውና ተዘንግተው ለህልፈት ተዳርገዋል:: እነዚህ የኪነጥበብ ሰዎች ለሀገር ትተውት ያለፉት ሥራ በርካታ ነው:: ነገር ግን የሚያስታውሳቸው እንብዛም ነው:: በተለይ አሁን ያለው ትውልድ ሥራቸውንም ሆነ ስማቸውን ሳያውቀው ሲቀር ማየት ሁሉንም ያስተዛዝባል:: የሚገባቸውን ክብር በጊዜያቸው ለመስጠትም እንቅፋት ይሆናል::

ከእነዚህ የሀገር ባለውለታ ከሆኑ የኪነ-ጥበብ ሰዎች መካከል አምሃ ተወዳጅ አንዱ ሲሆን፤ ለበርካታ ዓመታት በመድረክ አስተዋዋቂነትና በዘፈን ግጥም ደራሲነት የሚታወቅ ነው:: ይህ አንጋፋ የጥበብ ሰው ባለፈው ሳምንት አርብ በሞት ተለይቷል:: ብዙዎች ‹‹አፈ ማር›› እያሉ የሚጠሩት ይህ የመድረክ ንጉስ የተወለደውና ያደገው ጎንደር ከተማ ውስጥ ነው:: ገና የአራት ዓመት እምቦቀቅላ ሳለ ነው ወላጅ አባቱ እዛው ጎንደር በሚገኘው ባዕታ ቤተክርስቲያን መምህር ጋር ፊደል እንዲቆጥር የላኩት::

ቀላጣፊውና የቀለም ቀንዱ አምሃ የቤተ- ክነቱን ትምህርት አቀላጥፎ በመጨረስ ብዙ ሳይቆይ ነበር ዲያቆን መሆን የቻለው:: ይሁንና ወላጅ አባቱ አቶ ተወዳጅ ለትምህርት ያላቸው ጉጉት ከፍተኛ ስለነበርና ልጃቸውም ዘመናዊ እውቀት እንዲቀስም የሚፈልጉ በመሆናቸው ዲያቆን ሆኖ ብቻ እንዳይቀር በማሰብ ከባለቤታቸውና ከወዳጅ ዘመድ ጋር ተማክረው በፃድቁ ዮሐንስ ትምህርት ቤት አስገቡት::

በልጅነቱ ጨዋታና ዝላይ ይወድ የነበረው አምሃ በትምህርቱም ጎበዝ ተማሪ ነው:: ይህ ጉብዝናውም በጥቂት ዓመታት ውስጥ ስምንተኛ ክፍል እንዲያጠናቅቅ አግዞታል:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትምህርት ቤት የተከታተለ ሲሆን፤ ከትምህርቱ ጎን ለጎን የኪነ-ጥበብ ዝንባሌውን ከፍ የሚያደርጉ ተግባራትን ይከውናል:: ‹‹አባ ገርሜ›› በተባሉ ሰው አማካኝነት የተለያዩ ቴአትሮችን ለወላጆች ቀን በማሳየት የመምህራኑንና የወላጆችን ቀልብ መግዛት ችሏል:: በዚህ ሳያበቃም እንደሱ የጥበብ ፍቅር ካደረባቸው ተማሪዎች ጋር በመሆን ክረምት ክረምት የተለያዩ ቴአትሮችን እያጠና ወደተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በመዘዋወር ያቀርባል::

ብዙ ጊዜ አጃቢ ሆኖ የሚተውነው አምሃ፤ መሪ ተዋናይ ያለመሆኑ ነገር ያበሳጨው ነበር:: አንድ ቀን ግን ይህንን እውን የሚያደርግበትን እድል ያገኛል:: ይህም የአፄ ዮሐንስን ቴአትርን በኤርትራ ሊያሳዩ ይሄዱና የአፄ ዮሐንስን ገፀባህሪ የሚሰራው ልጅ ይታመማል:: ይህንን ጊዜ ታዲያ አዘጋጁ የኃይሌ ገሪማ ወላጅ አባት አባ ገሪማ ግራ ተገቡ፤ እጅግ ተጨነቁ፤ ሁኔታቸውን የተገነዘበው ቀልጣፋው አምሃም በድፍረት ያንን ገፀ-ባህሪ ወክሎ እንዲጫወት ፈቃቸውን ጠየቀ:: በወቅቱ አማራጭ ያልነበራቸው አባ ገሪማም ጥርጣሬ እያደረባቸው ‹‹እስቲ ሞክረው›› አሉት:: እሱ ግን ከጠበቁት በላይ ገፀ-ባህሪውን ሆኖ አስደመማቸው:: በአቀራረቡ እጅግ ተደንቀው እድሉን ሰጡትና ከጉድ እንዳወጣቸው ከአራት ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ‹‹አርሒቡ›› ፕሮግራም ላይ በቀረበበት ወቅት ተናግሯል::

ያቺ ቀን ታዲያ የሕይወቱ አቅጣጫ የቀየረች አጋጣሚ ፈጠረች:: ትኩረቱንም ከትምህርት ወደ ኪነት ዓለም እንዲያዘነብል ምክንያት ሆነች:: በኋላም ከብሔራዊ ቴአትር ቤት ባለሙያዎች ጋር በመሆን ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቴአትር በሚያቀርብበት ጊዜ በአባ ገሪማ አማካኝነት እድሉን አገኘና ወደ አዲስ አበባ መጣ:: ከብሔራዊ ቴአትር ታላላቅ ባለሙያዎች ጋር በመሆንም ለንጉሱ ባቀረቡት ቴአትርም ድንቅ ብቃቱን አሳየ:: በወቅቱ በልጅ እግሩ አምሃ አቀራረብ የተማረኩት ጃንሆይ አስጠርተውት አነጋገሩት፤ ሁኔታውን ተረድተው ጀነራል መርዕድ መንገሻ ወስደውት እንዲያሳድጉትና እንዲደግፉት አደራ ሰጡት::

ወጣቱ አምሃ ጀነራል መርዕድ ቤት እየኖረ ሳለም ጀነራሉ ገና እግራቸው ከቤት ሲወጣ ተከትሎ ክቡር ዘበኛ ሙዚቀኞች ጋር እየሄደ ይውላል፤ አብሯቸው ልምምድ ያደርጋልም:: አንድ ቀን አጋጣሚ ሆኖ የምድር ጦር ኦርኬስትራ ኮንጎ ለሚያደርገው የሙዚቃ ዘመቻና ቅስቀሳ ሥራ ዝግጅት እያደረገ ባለበት ወቅት የመድረክ አስተዋዋቂ ያጣል:: እናም ጨዋታ አዋቂው አምሃ መድረክ አስተዋዋቂ እንዲሆን ተመረጠ:: በዚያ መድረክም በእንግሊዘኛ ፣ አረብኛና ኪስህዋሊ ቋንቋዎችን አጥንቶ መድረኩን በተሳካ ሁኔታ መራ:: ይህቺም አጋጣሚ ሌላ እድል ነበረች:: ዓይኖቹን የገለጠባት ዕለት:: ስለዚህም በተለይ በአዲስ ዓመት ልዩ ዝግጅት ላይ በሚያቀርበው ማራኪ ሥራዎች ከፍተኛ ተቀባይነት እንዲያገኝ አግዛዋለች::

አንድ መድረክ ለማቅረብ ከልቡ ተጨንቆና ተጠቦ ዝግጅት ያደርግ እንደበርም የሚያውቁት ይመሰክራሉ፤ ይህም ታዲያ በወቅቱ ተፎካካሪ ከነበሩት እንደ ገዛኸኝ ደስታና ተስፋዬ ሳህሉ (አባባ ተስፋዬ) ጋር እኩል እውቅና እንዲያገኝ አግዞታል:: በተለይም በአስቂኝ ቀልዶቹና ለዛ ባለው ጨዋታው መድረኩን መቆጣጠርም ሆነ የታዳሚያንን ቀልብ መሳብ ለአምሃ ብርቅ አልነበረም:: በዘመኑ ትልቅ ከበሬታም ያገኘው በዚህ ምክንያት ነው:: እሱ ያልተገኘበትና ያልመራው መድረክ ይደምቅ የማይመስላቸው አድናቂዎቹ በየመድረኩ የሚያቀርበው ሥራ በተደጋጋሚ እንዲቀርብ በመጠየቃቸው የእውቅ ጫፍ ላይ እንዳደረሱት ይናገራል::

በኢትዮጵያ የኪነ-ጥበብ ታሪክ እንቁና ብርቅ አርቲስቶች በአዲስ ዓመት የሚያዘጋጁት ዝግጅት ዘርፉን በእጅጉ ያነቃቃ ብቻ ሳይሆን፤ በኢትዮጵያ ሙዚቃ እድገት ላይ አይተኬ ሚና የተጫወተ ጭምር እንደነበር እሙን ነው:: በተለይ ደግሞ ከ1950ዎቹ ጀምሮ እስከ 70ዎቹ መጀመሪያ ያሉት ተከታታይ ዓመታት አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግና በፉክክር ስሜት በርካታ ዘፈኖች እንደ መስከረም አደይ አበባ በየመድረኩ ይፈካሉ:: በወቅቱ የነበሩ የወታደርና የሲቪል የሙዚቃ ጓዶች የሚያደርጉት ‹‹የእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ›› ትንቅንቅ አዲስ ዓመትን በእጅጉ የሚያስናፍቅም ነበር:: በዋናነትም የክብር ዘበኛ፣ የምድር ጦር፣ የፖሊስና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ቤት (የአሁኑ ብሔራዊ ቴአትር) ለዚህ ፉክክር ዋንኛ ተሰላፊ ናቸው::

ለዚህ ታላቅ ፉክክር ሲባል ሙዚቀኞች፣ ድምጻውያን፣ የግጥምና ዜማ ደራሲዎች እና ተወዛዋዦች የአዲስ ዓመት ዝግጅታቸውን የሚጀምሩት ገና በግንቦት ወር ነበር:: ሩቅ ይመስላል:: ወራቱን በትጋት ለሚታትሩባቸው ለእነ አምሃ የመሳሰሉ ከያኒያን ግን ምንም ነው:: አንዱ ዜማ ሲያወጣ፣ ሌላው ግጥም ሲጽፍ፣ አንዱ ሲያቀናብር፣ ሌላው ሲለማመድ፤ እንደዋዛ መስከረም ከተፍ ይላል:: የአንዱ ክፍል የአንዱን ፈጠራ እንዳይቀማም ነቅቶ መጠበቅ ግድ ነው:: ከመስከረም ዋዜማ ጀምሮ በየተራ በሚቀርበው ዝግጅት አሸናፊ ሆኖ፤ የንጉሱን ሽልማት፣ የታዳሚውን የሞቀ አቀባበልና የጋዜጦቹን ሙገሳ ለማግኘት በር ዘግቶ መትጋት የየክፍሉ ሙዚቀኛ ግዴታ ነው::

በዚህ መንገድ ሙዚቃም ዛሬ አንዳንዶች እንደሚያደርጉት “ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ” እንደሚባለው ሳይሆን በጥሩ ቅመምና ለዛ ተሞሽራ አድማጭ ጆሮ ትደርሳለች:: ዘመኗም በጊዜ የማይሟሸሽ፣ በቦታ የማይጠለሽ ሆኖ፤ ይኸው ዛሬም ሳንታክት የትናንቶቹ ሙሾሮች አላረጁብንም:: ላይናችን አልደበዘዙም፤ ለጆሯችንም አልጎረበጡም:: ፉክክሩ በትልቁ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ቤት ነው:: ንጉሱና የልዑላን ቤተሰቦች፣ ባለስልጣናት፣ ታላላቅ መኮንኖች፣ ጋዜጠኞችና አዳራሹን እንደ ንብ ከአፍ እስከ ደፉ የሞሉት ታዳሚያን ጆሯቸውን አንቅተው የሚሆነውን ለማየትና ለመስማት በደስታ የሚጠብቁት:: የየክፍሉ ሙዚቀኞች፣ ተወዛዋዦችና ድምጻውያን በበኩላቸው በተጠንቀቅ ቆመው ተራቸውን በታላቅ ጉጉትና መረበሽ የሚያዳምጡት::

እንግዲህ በዚህ ቀውጢ ሰዓት ነው፤ መድረክ መሪዎች ብቅ የሚሉት:: ለወራት የተደከመበት ማዕድ ውጥንቅጡ እንዳይወጣ፤ እየበለቱና እያዋዙ አይተኬ ሚናቸውን የሚወጡት:: “ከፍትፍቱ ፊቱ” እንደሚባለው መድረክ መሪዎች የዝግጅቱ ፊት አውራሪ ናቸው:: ደምቀው ማድመቅ፣ ስቀው ማሳቅ የተፈቀደላቸው:: ታዳሚ ዝግጅቱን በታላቅ ጉጉትና ደስታ ይጠብቅ ዘንድ ቁም ነገሩን እያዋዙ፣ የደረቀውን እያለዘቡ ንቁ ታዳሚን ከከያኒው የሚያገናኙ ሀዲዶች:: ቅንጣት ክፍተትን በፈጣን ክህሎታቸው እያሻገሩ ከትልቅ ማዕድ የሚያደርሱ ድልድዮች::

የጥንቱ የአዲስ ዓመት የወታደር ኦርኬስትራዎችና የሲቪል ሙዚቀኞች ፉክክር፣ ከሚሰሙት አዳዲስ ዘፈኖች ባሻገር የየክፍሎቹ መድረክ መሪዎች ዝግጅትም በጉጉት የሚጠበቅ ነው:: መድረክ መሪዎች አንዱን ክፍል ከሌላው ለማስበለጥና ውድድሩን ለመጋጋል በእጅጉ ይተጋሉ:: በዚህ ምክንያት ፉክክሩ በድምጻውያኑ መካከል ብቻ ሳይሆን በመድረክ አስተዋዋቂዎችም ጭምር ይሆናል:: “ማን ምን አለ” የሚለውን ለመስማት ታዳሚውም በላቀ መቁነጥነጥ ጆሮውን እንደ አንቴና ይቀስራል:: በድንቅ የመድረክ መሪነታቸው ታውቀው ለብዙዎች አርአያ እስከ መሆን ከደረሱት መካከል ደግሞ የምድር ጦሩ አምሃ ተወዳጅ አንዱ ነው::

አምሃ ተወዳጅ በዚህ ክፍል በሚሰራበት ወቅት አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር በመድረክ ድምቀታቸው ከሚናፈቁ አስተዋዋቂዎች መካከል ዋንኛው ነው:: ግን ደግሞ እንደ ክብር ዘበኛ መድረክ መሪዎች ሁሉ ታዲያ መድረክ መሪ ብቻ አይደለም፤ የተዋጣለት የግጥምና ዜማ ደራሲም ጭምር እንጂ! ታምራት ሞላ፣ ሐብታሙ ሽፈራው፣ አባይ በለጠ፣ ፀዳለ ገብረ ማርያምና ሌሎች ግጥምና ዜማ ድርሰቱን ካበረከተላቸው መካከል ተጠቃሽ ናቸው::

ተወዳጁ አርቲስት ከመድረክ ሥራው ባሻገር የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በ1957 ዓ.ም ሲመሰረት ‹‹ሙዚቃን በመስኮት›› በኋላም ‹‹ህብረት ትርዒት›› የተሰኘውን ፕሮግራም በማቅረብ የመጀመሪያው ሰው ነበር:: በየሳምንቱ ማክሰኞ በሚቀርበው በዚህ የሙዚቃ ግብዣ ፕሮግራም ላይም ከመድረክ ባለፈ ሁሉም በየቤቱ የሚናፍቀው ሰው እንዲሆን አድርጓል:: እሱ ግን የመድረክ ሥራው ከታዳሚን ጋር በቀጥታ የሚያገናኘው በመሆኑ ከቴሌቪዥኑ ይልቅ የመድረኩን ሥራ እጅግ ይወደው እንደነበር በአንድ ወቅት በሰጠው ቃለ-ምልልስ መስክሯል::

በ1977 ዓ.ም በኢትዮጵያ ከተከሰተው ድርቅ ጋር ተያይዞ አምሃና የሙያ አጋሮቹ በመተባበር በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ገቢ ማሰባሰቢያ የሙዚቃ ሥራ ሰሩ:: አምሃ ያንን ዝግጅት ከማስተባበር ባለፈ ‹‹ የብሩ ተስፋ እሸት›› የተሰኘውና ሃመልማል አባተ፣ መልካሙ ተበጀ፣ ኤፍሬም ታምሩን የመሳሰሉ ታዋቂ ሙዚቀኞች ያቀረቡትን ዜማና ግጥም ላይ ተሳትፎ አድርጓል:: ይህ የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች አንድነት ማህበር በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች 12 ድምፃውያን እና ከሮሃና ዋሊስ ባንድ ጋር በመተባበር ያዘጋጁት ሙዚቃ በካሴት ታትሞ በመሸጥ ከፍተኛ ገቢ ያስገኘም ነበር::

የዛሬው ባለውለታዎቻችን ዓምድ ተረኛ አምሃ በማህበሩ ውስጥ በሚሰራበት ጊዜም አዳዲስ ዘፈኖች ታትመው ገበያ ላይ ከመዋላቸው በፊት የመመርመር፣ የማሳለፍና የመጣል ኃላፊነት ነበረው:: በዚህ ወቅት ታዲያ አምሃ ሙዚቀኞቹ በስራቸው ውስጥ ስለሃገርና ህዝብ የሚቀነቅኑ ዜማዎች እንዲካተቱ በማስገደድ እና ጫና በማሳደር ይታወቅ ነበር:: ዛሬ ድረስ ደግመን ደጋግመን የምናዜማቸውና በተለይ ሃገር ፈተና ውስጥ በወደቀችበት ጊዜ ሁሉ የምንመርጣው ሃገር ተኮር ዘፍኖች በዚያ ወቅት የተዘፈኑ ናቸው::

መድረክ አስተዋዋቂውና የዜማና ግጥም ደራሲው አምሃ ተወዳጅ ከአምስት አስርት ዓመታት በላይ ሀገሩን በጥበብ ሲያገለግል ቢቆይም ኢኮኖሚው ግን እንደብዙዎቹ አርቲስቶች ጥሩ የሚባል አልነበረም:: በተለይም ጡረታ ከወጣ በኋላ ብዙም መድረክ የማግኘት እድሉን አላገኘም:: ከአራት ዓመታት በፊት ጀርመን ድረስ በመሄድ ህክምናው ሲከታተል የቆየው ይህ አንጋፋ አርቲስት ታላቅ ሥራዎቹን ለሀገር ትቶ ከሰሞኑ ማለፉ ሲሰማ ለብዙ የሙያ አድናቂዎቹ ቅስም ሰባሪ ነበር:: ሆኖም ታሪክ ሰሪ አይሞትምና የማይቀበረውን ስሙን ተክሎ ተሰናብቷል::